


የግብ ረገብ ትምህርት

የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ

2ኛ ክፍል







የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር

ለመጽሐፉ መደረግ ያለበት ጥንቃቄ

ይህ መጽሐፍ የትምህርት ቤታችሁ ንብረት ከመሆኑም በተጨማሪ በቀጣይ ታናናሽቻችሁ የሚማሩበት ስለሆነ መጽሐፉ እንዳይቀደድ ወይም እንዳይበላሽ ተገቢ የሆነ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

ለጥንቃቄ የሚረዱ የሚከተሉትን 10 ነጥቦችን ልብ በሉ።

- መጽሐፉን እንደ ፕላስቲክ፣ የቆዩ ጋዜጦች ወይም መጽሔቶችን በመሳሰሉት ሸፍናችሁ ያዙ።
- ሁልጊዜ መጽሐፉን በደረቅ ቦታ አስቀምጡ።
- መጽሐፉን በምትጠቀምበት ጊዜ እጆቻችሁ ንጹሕ መሆናቸውን ማረጋገጋጥ ያስፈልጋል።
- በሽፋኑ ወይም በገጾቹ ላይ አለመፃፍ።
- መጽሐፉ እንዳይበላሽ ቁራጭ ወረቀት ወይም ካርቶን መጠቀም።
- በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ምስሎች ወይም ገጾችን ፈጽሞ አለመቅደድ ወይም አለመገንጠል፣ የተቀደዱ ገጾች ካሉ በመለጠፍ ወይም በመጠገን መጠቀም።
- መጽሐፉን በትምህርት ቤት ቦርሳ ውስጥ በጥንቃቄ ማስቀመጥ፣

- መጽሐፉን ለሌላ ሰው ስታውሱ በጥንቃቄ እንዲያዝ መንገር::
- አዲስ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ስትጠቀሙ በጀርባው አስተኝተው ይጠቀሙ::
- በአንድ ጊዜ ጥቂት ገጾችን ብቻ ክፈቱ:: በአንድ ላይ የተጣበቁ ገጾችን ጠርዙን ተጭናችሁ በትንሹ ግለጡ::



ግብረ ገብ ትምህርት

የተማሪ መጽሐፍ

2ኛ ክፍል

ደራሲ፡- ተስፋዬ ጂማ (ፒኤችዲ)

ምናለ አዱኛ/ ረዳት ፕሮፌሰር/

አዘጋጆች፡- አለማየሁ ነጋሽ (ዶክትሬት)

ቃለ ወንጌል ምናለ (ዶክትሬት)

ሙሉጌታ ያየህ (ዶክትሬት)

አስማሚዎች፡ ታድዮስ ጌታሁን/ ኤም.ኤ/

አሸኮ ጃሎ/ ኤም.ኤ/

ገላጭ፡ - ኤልዛልሞን ጌቱ (ኤም.ኤስ.ሲ.)

አቀማመጥ ዲዛይነር፡- ናትናኤል ውብሸት

ይዘት አርታኢ፡- ሀብታሙ ቶማስ (ኤም.ኤ)

የቋንቋ አርታኢ፡-እናኑ ብዙነህ

የሳይንስ እና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ

የቅጂ መብት

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በኩል በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ሲሆን የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር እና የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀ ሲሆን አጠቃላይ የሕትመት ወጪው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ተሸፍኗል።

የመጽሐፉ ሕጋዊ ቅጂ ባለቤት @ 2014 ዓ.ም የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር እና የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ናቸው።

መግቢያ

ኢትዮጵያ በልዩ እሴቶቿ፣ በማህበራዊ እና ባህላዊ ቅርሶቿ በሰፊው የምትታወቅ ጥንታዊ ሀገር ነች። እነዚህም ለአመታት ለመንግስት እና ለህብረተሰቡ አቅርቦት እና ቀጣይነት አጋዥ ነበሩ። በዚህ ረገድ፣ እነዚህ እሴቶች እና ባህሪያት ተጠብቀው እንዲቆዩ፣ እና ለአዲሱ ትውልድ እንዲተላለፉ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው።የግብረ ገብ ትምህርትን እንደ ልዩ እና የተለየ የትምህርት ዓይነት በትምህርት ቤት ሥርዓተ-ትምህርት ውስጥ ማካተት ማህበረሰባችን የሚያከብራቸውን እሴቶች እና ደንቦች ለማስተማር እና ለማስተላለፍ ያስችለናል። ዘመናዊ የግብረ ገብ ትምህርት የአንድን ማህበረሰብ መልካም እና ትክክለኛ ባህሪያትን ለዜጎቹ የማስተላለፍ ተግባር ነው።

እውነት ነው ኢትዮጵያ የተለያዩ ብዙሀን የአካባቢ ቋንቋዎች፣ የማህበራዊ እና የባህል ልዩነቶች በትልቁ ጎልተው የሚታዩባት ሀገር ነች። በረጅም ጊዜ ማህበራዊ መስተጋብር እና ትስስር፣ በመላው ሀገሪቱ ያሉ ኢትዮጵያውያን ግን በተለምዶ የሚጋሯቸው እና እንደ ማህበረሰብ የሚንከባከቧቸው የሞራል እሴቶችን አዳብረዋል። ታላላቆቻችንን ማክበር፣ መልካም ጉርብትና፣ እንግዳ ተቀባይነት፣ ማህበራዊ መደጋገፍ እና መረዳዳት በሀገሪቱ በስፋት የሚተገበሩ እሴቶች ናቸው።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን በአገሪቱ ውስጥ የሚታዩ አዝማሚያዎች የወጣቶች ሥነ ምግባራዊ ባህሪ ማሽቆልቆሉን ያመለክታሉ፡፡ የሥነ ምግባር ትምህርት መመሪያ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ አስፈላጊ ሆኗል፡፡ በዚህ መሰረት የግብረ ገብ ትምህርት ርእሰ-ትምህርት በትምህርት ቤት ስርአተ-ትምህርት ውስጥ ማካተት በሥነ ምግባር የታነጹ ዜጎችን ለማፍራት ያስችላል፡፡ የወቅቱ ትምህርት ብልህ የሚያደርግ ብቻ ሳይሆን በሥነ ምግባራቸው ጨዋ የሆኑ ዜጎችን ለማፍራት የተዘጋጀ ነው፡፡

የ 2 ኛ ክፍል ሥርዓተ-ትምህርት ወሳኝ የሆኑ ማህበራዊ በጎነቶች እና እሴቶችን በመገንባት ሂደት ውስጥ ቁልፍ በሆኑ የግብረ ገብ እሴቶች ላይ ያተኩራል፡፡

የይዘት ግንባታው በቀደመው ክፍል ከተሸፈኑ ጭብጦች ሲሆን ግን አዳዲሶችንም ያስተዋውቃል፡፡ አጠቃላይ አላማው ያለፉትን የትምህርት ይዘቶች ማጠናከር እና ተማሪዎችን ተጨማሪ ፅንሰ-ሀሳቦችን ማስተማር ነው፡፡

በተለይም የዚህ ክፍል ይዘት ከሌሎች ዜጎች ጋር አዎንታዊና ማህበራዊ ግንኙነቶችን ለማመቻቸት በግለሰብ ሁኔታዎች ላይ አፅንዖት ይሰጣል፡፡ በመጀመርያው ምዕራፍ ውስጥ ያለው ራስን ማክበር ለሥነ ምግባራዊ ባህሪ እና ለግለሰቦች ሥነ-ምግባራዊ

እድገት መሠረት ነው። ሌሎችን ማክበር ራስን ከማክበር ይጀምራል። በተጨማሪም የተማሪ ባህሪያት እውነትን እና ታማኝነትን፣ እኩልነትን እና ፍትህን፣ ለጋራ ጥቅም መቆርቆር እና አዎንታዊ ማህበራዊ ግንኙነቶችን ለማራመድ በሚደረጉ ተግባራት መመራት አለባቸው። የእነዚህ የሥነ ምግባር ሁኔታዎች በግለሰብ ደረጃ ማዳበር በተጨማሪም ከሌሎች ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲኖር እና በህብረተሰቡ ውስጥ መግባባት እንዲፈጠር አስተዋጽኦ ያደርጋል።

ማውጫ

መግቢያ v

ምዕራፍ አንድ 1

ራስን ማክበር እና ደህንነትን መጠበቅ 1

1.1 ራስን ማክበር 1

1.2 ራስን ማክበር አስፈላጊነት 5

1.3 ራስን የማክበሪያ መንገዶችን መገንባት 7

1.4 ሰላም/ደህንነት መጠበቅ 13

1.5 ልጆች ደህንነታቸውን እንዲጠብቁ የሚረዱ መንገዶች 14

ምዕራፍ ሁለት 24

እውነትን እና ታማኝነትን መሻት ወይም መፈለግ 25

2.1 የእውነት እና የታማኝነት ትርጉም 25

2.2 የእውነት እና የታማኝነት ዓይነቶች 26

2.2.1 እውነትን መናገር 26

2.2.2 ቃልን መጠበቅ 27

2.2.3 አትስረቅ ወይም አታጭበርብር 28

2.3 የእውነተኛ እና ታማኝ ሰው ብቃት 29

2.4 የእውነት እና ታማኝነት አስፈላጊነት 30

2.5 እውነተኛ እና ሐቀኛ የመሆን ጥቅም 33
2.6 የእውነት እና የታማኝነት አለመኖር ውጤቶች 36
ምዕራፍ ሶስት 42
ፍትህ 42
3.1 የፍትህ ትርጉም 42
3.1.1 የፍትሃዊነት ጽንሰ-ሐሳብ 44
3.2 የፍትሃዊነት አስፈላጊነት 47
3.3 ፍትሃዊ አስተሳሰብ ያለው ሰው ባህሪያት 48
3.4 የፍትህ መጓደል ውጤት 50
3.5 ኢ-ፍታዊነትን መቃወም 52
ምዕራፍ አራት 58
አወንታዊ ማህበራዊ መስተጋብር 58
4.1 አወንታዊ ማህበራዊ ግንኙነት ትርጉም 58
4.2 ጠቃሚ አወንታዊ መንገዶች እና ማህበራዊ ግንኙነቶች 68
4.3 አወንታዊ ወይም መልካም ማህበራዊ ግንኙነት አስፈላጊነት 69
4.4 መልካም ማህበራዊ ግንኙነት መሰናክሎች 70
ምዕራፍ አምስት 76

ለጋራ ጥቅም ትኩረት መስጠት 76
5.1 የጋራ ጥቅም ትርጉም 76
5.2 ለጋራ ጥቅም የማሰብ አስፈላጊነት 80
5.3 ለሌሎች ደህንነት መኖር/Altruism/በጎነት 82
5.4 ግለሰባዊነት እና የጋራ ጥቅም 85
5.5 የጋራ ጥቅም አካላት 86
5.5.1 የህዝብ ደህንነት 86
5.5.2 የህዝብ ሀብትን በጥበብ መጠቀም 87
5.5.3 አካባቢን መጠበቅ 89
5.6 ለጋራ ጥቅም እንቅፋቶች ወይም ተግዳሮቶች 91
ምዕራፍ ስድስት 95
ባህላዊ ቅርሶች 95
6.1 የባህል እና ቅርሶች ትርጉም 95
6.2 የባህል ቅርስ ዓይነቶች 98
6.3 የባህል እና ቅርሶች መጠበቂያ መንገዶች 105
6.4 የባህል ቅርሶች አስፈላጊነት 107

ምዕራፍ አንድ

ራስን ማክበር እና ደህንነትን መጠበቅ

ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

•ራስን የማክበር ጽንሰ-ሀሳብ ታብራራላችሁ፡፡

• ራስን የማክበር አስፈላጊነት ዋጋ ትሰጣላችሁ፡፡

• ለራስ ክብርን የሚያሳዩ መንገዶችን ትለያላችሁ፡፡

• ራስን ማክበር እንዴት መገንባት እንደሚቻል ትገልጻላችሁ ፡፡

• ራስን ከአካላዊ እና ስነ-ልቦናዊ ጎጂ ከሆኑ ድርጊቶች እንዴት መጠበቅ እንደሚቻል ታሳያላችሁ፡፡

1.1 ራስን ማክበር

ውድ ተማሪዎች፣ ራስን ማክበር ማለት ምን ማለት ነው? መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ ንገሯቸው፡፡

ራስን ማክበር ማለት፡- ራስን መውደድ፣ በጥንቃቄ ራስን መንከባከብ፣ በራስ መደሰት ወይንም በራስ መተማመን ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም ራስን ማክበር ማለት አንድን መልካም ምግባር በኩራት፣በደስታ ወይንም በክብር የመፈፀም ስሜት ነው፡፡



መልካም ምግባርን በስራት ወይንም በክብር የመፈፀም ሰሜት

ተግባር 1

ከላይ ያለው ሥዕል ምንን ያሳያል? መልሶቻችሁን በጥንድ /በጋራ ተወያዩ እና ለክፍሉ ተማሪዎች ያብራሩ።

ቤተሰብን እና ጎረቤትን መርዳት

ሀና የምትኖረው ድልፋና በምትባል ትንሽ መንደር ነው። አንድ ቀን ለእናቷ ጨው፤ ቡና እና ሽንኩርት ልትገዛ ወደ ገበያ ስትሄድ ጎረቤታቸው እመቤት አልማዝ ልጅ የሌላት በመሆኗ የሀናን እርዳታ ፈለገች እናም የሃናን እናት ሃና እንድትረዳት ጠየቀቻት።

ሃናም የእናቷን ጓደኛ እና የጎረቤታቸውን ጥያቄ በደስታ ተቀብላ እመቤት አልማዝ የምትፈልገውን ለመግዛት ወደ ገበያ ሄደች።



(እማማ አልማዝ የሃናን እናት ድጋፍ ስትጠይቅ)

ቤተሰብ እና ጎረቤትን መርዳት

ተግባር 2

ከላይ ያለው ሥዕል ምን ያሳያል?

ለራስ ክብር መስጠት ያለው ፋይዳ

ዮናታን እና ኡፋይሳ የትምህርት ቤት ጓደኛሞች እና የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። ትምህርት ቤታቸው በወር አንድ ጊዜ የባህል ቀንን በማስመልከት ለትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ፕሮግራም ያዘጋጃል። በዚህ ዕለት ዮናታን እና ኡፋይሳ የባህል ልብሳቸውን ለብሰው ለዕለቱ ያዘጋጁትን መዝሙር በመልካም ስነምግባርና በታላቅ ኩራት ለታዳሚዎች አቀረቡ። ከታዳሚዎች እና ከትምህርት ቤቱ ላቅ ያለ ምስጋና በማግኘታቸው በራሳቸው መደሰትና በራስ መተማመናቸው እየጨመረ ሄደ። በመጨረሻም ዮናታን እና ኡፋይሳ በተለያዩ ቦታዎች በሚዘጋጁ ባህላዊ በዓላት ላይ መዝሙሮችን ማቅረባቸውን ቀጠሉ።



የባህላዊ በዓላት አከባበር

ተግባር 3፡

ከላይ ያለው ሥዕል ምን ያሳያል?

1.2 ራስን ማክበር አስፈላጊነት

ራስን ማክበር አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም በሌሎች ዘንድ አክብሮትን እንድናገኝ እና በሕይወታችን ስኬታማ እንድንሆን የሚያስችል በራስ መተማመን ይሰጠናል።

ራስን ማክበር ማለት ለምን አላማ እንደቆሙ እና እሴቶቻችን ምን እንደሆኑ ማወቅ ማለት ነው። በተጨማሪም ሁለቱንም ጠንካራ ጎኖቻችንን እና ድክመቶቻችንን መቀበል ማለት ነው።

አክብሮት በሁለት መንገድ ነው፣ ሌሎች ሰዎችን እንደሚገባቸው ክብር ተሰጥቶአቸው ካልተያዙ ፣ራስን ብቻ ማክበር ወይም ለሌላው ክብር አለመስጠት በሌሎች ሰዎች ዘንድ ተቀባይነትን ያሳጣል። ስለዚህ ለሌሎች ሰዎች ክብርን ስንሰጥ እኛም እንከበራለን ማለት ነው።

ተግባር 4፡ ከላይ ባለው አንቀፅ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያዩ

1. እራስን የምናከብርበት መንገድ የትኛው ነው?
2. ቤተሰቦቻችሁን የምታከብራቸው በምን በምን መንገድ ነው?

3.በአካባቢያችሁ የሚገኙ አዛውንቶችን ስታከብሩ ምን ታደርጋላችሁ?

4. ለራስ ክብር መስጠት ምን ጥቅም አለው?



ራስን እና ሌሎችን ማክበር

ተግባር 5

ከላይ የሚታዩ ስዕሎች ምንን ያሳያሉ?

1.3 ራስን የማክበሪያ መንገዶችን መገንባት

ለራስ አክብሮት ለመገንባት ብዙ መንገዶች አሉ። ለምሳሌ፣ የሚከተሉት ሥዕሎች እና ተግባራት ራስን የመገንባት ልምድ ናቸው።

የትምህርት ቤት ደንቦችን በመከተል

መምህሩ በክፍል ውስጥ የሚያወጧቸው ህጎች እና መመሪያዎች፡-

- ወደ ትምህርት ቤት ስትሄዱ የደምብ ልብስ መልበስ።
- በክፍል ውስጥ ጥያቄዎችን ለመመለስ እጆቻችሁን ማንሳት።
- መምህራን ወደ ክፍል ሲገቡ ከመቀመጫችሁ መነሳት።



(የደምብ ልብሳችሁን መልበስ)



(በክፍል ውስጥ ጥያቄዎችን ለመመለስ እጆቻችሁን ማንሳት)



(የክፍል ስራ ሲሰሩ)



(ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሆነው መምህራቸው እስኪገባ ድረስ መጠበቅ)



(መምህራን ወደ ክፍል ሲገቡ ከመቀመጫችሁ መነሳት)

ተግባር 6

ከላይ ያሉት ሥዕሎች ምንን ያሳያሉ?

ማላንቼ እና ኡፋይሴ

ማላንቼ እና ኡፋይሴ ጎረቤታሞች ናቸው። ሁለቱም የ2ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። አንዳንድ ጊዜ በሳምንቱ መጨረሻ ማላንቼ ኡፋይሴን እና ቤተሰቦቿን ወደ ወላጆቿ ቤት ወስዳ ቡና እና ምሳ ትጋብዛታለች። በተመሳሳይም ኡፋይሴ ማላንቼን እና ቤተሰቧን በወላጆቿ ቤት አብሯቸው ቡና እና እራት ጋበዘቻቸው። በመጨረሻም ማላንቼ እና ኡፋይሴ ከራሳቸው አልፈው ቤተሰቦቻቸውን በማቀራረባቸው እጅግ ተደሰቱ።



(ማላንቼ ኡፋይሴን እና ቤተሰቦቿን በወላጆቿ ቤት ስትጋብዝ)



(ኡፋይሴ ማላንቼን እና ቤተሰቦቿን ስትጋብዝ)

ተግባር፡ 7

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከላይ የተጠቀሱ ስዕሎችን እና ታሪኮችን መሰረት በማድረግ በቡድን ተወያዩ

አክባቢያችሁን መንከባከብ

ራሳችሁን መንከባከብ ማለት ቤታችሁንና አካባቢያችሁን መንከባከብ ማለት ነው። እራሳችሁን ካልተንከባከባችሁ ደግሞ ቤታችሁንና አካባቢያችሁን መንከባከብ አትችሉም። ስለዚህ እራሳችሁን፣ ቤታችሁን እና አካባቢያችሁን በሚያምሩ ነገሮች ስታስጌጡና ስትንከባከቡ ለራሳችሁ እና ለአካባቢያችሁ የምትሰጡት ክብር መልካም ባህሪ እንዳላችሁ ያመላክታል።



ህፃናት አከባቢያቸውን ሲንከባከቡ::

ተግባር 8

ከላይ ያለው ሥዕል ምንን ያሳያል?

1.4 ደህንነትን ጠብቆ መቆየት

ደህንነትን ጠብቆ መቆየት ማለት ራስን ከሚጎዱ ማኛውም ነገሮች መጠበቅ ማለት ነው። ደህንነት ማለት ከአደጋ ነጻ መሆን ማለት ነው። ደህንነትን መጠበቅ ከአደጋ መራቅ እና እራስን ከማንኛውም ጉዳት መጠበቅ ነው። ካልተጠነቀቅን ሊጎዱን፣ ሊያሰናከሉ ወይም ሊያቆስሉን የሚችሉ ብዙ ነገሮች አሉ።ስለዚህ ሁልጊዜ ደህንነታችን ተጠብቆ ለመኖር በቤት፣ በትምህርት ቤት፣ በመንገድ ላይ እና በመሳሰሉት አካባቢዎች የምንችለውን ሁሉ ጥረት ማድረግ እና ሁሉንም የደህንነት ደንቦችን እና መመሪያዎችን መከተልና ተግባራዊ ማድረግ ይኖርብናል።

ተግባር 9

(የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያዩ)

1. በቤታችሁ ውስጥ ደህንነታችሁን እንዴት መጠበቅ ትችላላችሁ?
2. በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ደህንነታችሁን ለመጠበቅ ምን ታደርጋላችሁ?

1.5 ልጆች ደህንነታቸውን እንዲጠብቁ የሚረዱ መንገዶች

ልጆች ደህንነታቸውን እንዲጠብቁ የሚረዱ ብዙ መንገዶች አሉ። ልጆች ማወቅና ማድረግ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች የሚከተሉት ናቸው።

- የቤትና የዱር እንስሳትን ሲመገቡ፣ ሲተኙ እና ከልጆቻቸው ጋር ሲሆኑ አለማሳደድ።
- በመዋኛ ገንዳ ውስጥ በጭራሽ ብቻችሁን አለመዋኘት።
- መንገድ ከጠፋባችሁ ወዲያውኑ እርዳታ መጠየቅ።
- ብቻችሁን የመኪና መንገድ አለማቋረጥና ለእግረኛ በተዘጋጀው መንገድ ላይ መጓዝ።
- መኪናዎች በሚያልፉበት ዋና መንገድ ላይ ምንም አይነት ጫወታ አለመጫወት።
- በሹል ወይም ስለታማ በሆኑ ነገሮች አለመጫወት።



አባት ለልጆቹ የደህንነት ምክሮችን ሲሰጥ።



(ቤተሰቡ ለጤና ተስማሚ የሆኑ ምግቦችን እየተመገቡ ናቸው)



(ወንዱ እና ሴቷ ልጅ ከእናታቸውና ከአባታቸው ጋር ብስክሌት ሲነዱ)

ተግባር 10

ከላይ ባሉት ሥዕሎች መሠረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ እና መልሶቻችሁን በደብተራችሁ ላይ ፃፉ።

1. ከላይ ያለው ሥዕል ምንን ያሳያል?
2. ጤናማ የሆኑ ምግቦች ደስተኛ ለመሆን የሚረዱት በምን መንገድ ነው?
3. ከዚህ በላይ ያሉት የደህንነት መጠበቂያ መንገዶች ደህንነታችሁን እና ጤነኛ እንድትሆኑ የሚረዳችሁ እንዴት ነው?

በሽታን መከላከል እና ደህንነትን መጠበቅ

❖ ከበሽታ ለመከላከል እና ደህንነታችሁን ለመጠበቅ የሚከተሉትን ቅድመ ጥንቃቄዎች ማድረግ አለባችሁ።

- ከመጸዳጃ ቤት ከተመለሳችሁ በኋላ ፣
- አፍንጫችሁን ካጸዳችሁ በኋላ፣
- ምግብ ከመብላታችሁ በፊት እጆቻችሁን በሳሙና መታጠብ አለባችሁ።
- ኮፍያዎችን፣ ማበጠሪያዎችን፣ የጥርስ ብሩሾችን ወይም ሌሎች የግል ቁሳቁሶችን ከሌሎች ልጆች ጋር አለመጋራት።
- በምታስሉበት ወይም በምታስነጥሱበት ጊዜ አፋችሁን በእጆቻችሁ መሸፈን ።
- የሌሎችን ልጆች ከሰውነት የሚወጡ ፈሳሾችን አለመንካት።

ተግባር 11

ከታች ከተገለጹት ሥዕሎች ምን ይማራሉ?



ልጆቹ ከጨዋታ በኋላ እጃቸውን ሲታጠቡ



ልጆች የራሳቸውን ማንኪያ ሲጠቀሙ



ልጆቹ በሚያስነጥሱበት ጊዜ አፋቸውን ይሸፍናሉ

ተግባር 12

ከሚከተሉት ውስጥ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ያልተጠበቀ ልጅ ባህሪን የሚያሳየው የትኛው ነው?

1. **ብቻውን የሚዋኝ፡፡**

2. **የሌሎችን ልጆች ደም እና ሽንት የሚነካ::**

3. **በሹልና ስለታማ መሳሪያዎች የማይጫወት፡::**

4. **የሌሎችን ኮፍያ፣ ማበጠሪያ እና ማንኪያ የሚጋራ፡፡**

5. መኪናዎች ባሉበት መንገድ ላይ ብቻውን አቋርጦ የማይጫወት ወይም የማይያልፍ።

6. እጆቹን ከሸንት ቤት ቦኋላ የማይታጠብ።

7. ከወላጆቹ ጋር በግልጽ አይነጋገርም።

8. እንስሳትን አያባርርም ወይም አይረብሽም።

9. የራሱን ወይንም የወላጆቹን ስልክ ቁጥር የማያውቅ።

ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ ውስጥ ደህንነቱ የተጠበቀ ልጅ እና ደህንነቱ ያልተጠበቀ ልጅ ባህሪያት ለይታችሁ ፃፉ።

ደህንነቱ የተጠበቀ ልጅ ባህሪያት	ደህንነቱ ያልተጠበቀ ልጅ ባህርያት

የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ልጆች እራሳቸውን እንዲገነዘቡ፣ እራሳቸውን እንዲያውቁ እና ሌሎችን እንዲያከብሩ ስለሚረዷቸው ለራስ ማክበር፣ ስለራስ ክብር አስፈላጊነት፣ ለራስ ክብር ስለመስጠት፣ ለራስ ክብርን መገንባት እና ደህንነትን ስለመጠበቅ ተምረዋል።

ይህ ማለት እራሳቸውን የሚያውቁ ልጆች የሌሎችን ልዩነት በቀላሉ ማክበር፣ ማድነቅ እና መቀበል እና ሽማግሌዎችን በአክባቢያቸው ማክበር ይችላሉ።

ከዚህም በላይ ልጆች ከማንኛውም አደጋ መጠበቅ እንዳለባቸው ተምረዋል ስለዚህ ቤተሰብ፣ ትምህርት ቤት እና ማህበረሰብ ከማንኛውም አደጋ እንዲጠበቁ ማስተማር አለባቸ። ልጆች ቤተሰባቸውን፣ አስተማሪዎቻቸውን ማዳመጥ እና የተማሩትን ህግ ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው።

የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

I. አረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ 'እውነት' ትክክል ካልሆነ ደግሞ 'ሐሰት' ብላችሁ ደብተራችሁ ላይ ጻፍ።

1. ቤተሰብን እና ማህበረሰብን መንከባከብ አስፈላጊ አይደለም።
2. የግለሰባዊ ልዩነቶች መከባበር በሰላም እንድንኖር ይረዳናል።
3. ራስን ማክበር በራስ የመተማመን ስሜትን ይቀንሳል።
4. ራስን ማክበር ማለት ጥንካሬዎን እና ድክመትዎን መቀበል ማለት ነው።
5. ሽንት ቤት ከተጠቀማችሁ በኋላ ምን ጊዜም እጃችሁን መታጠብ አለባችሁ።

II. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡ አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

1. ከሚከተሉት ውስጥ ለራስ ክብርን የማሳየት እና የመገንባት መንገድ ያልሆነው የትኛ ነው?

ሀ. የትምህርት ቤቱን ህጎች መከተል

ለ. ልዩነቶችን ማድነቅ

ሐ. አንድ ሰው ለሚወደው እና ለሚጠላው ዋጋ መስጠት

መ. በክፍል ውስጥ በመምህራችሁ ተዘጋጅተው የተለጠፉትን ህግጋት አለማክበር

2. ከሚከተሉት ውስጥ የሚያስደስታችሁ የትኛው ነው?

ሀ. እራስን ማክበር

ለ. ሌሎችን ማክበር

ሐ. በደህንነት መቆየት

መ. ከላይ ያሉት ሁሉም መልስ ናቸው

3. ከሚከተሉት ውስጥ ክብር የሚገባው ለየትኛው ነው?

ሀ. ለአረጋውያን

ለ. ለታናሽ ወንድም

ሐ. ላንተ/ቺ የቅርብ ጓደኛ

መ. ከላይ ያሉት ሁሉም መልስ ናቸው

3. ከሚከተሉት ውስጥ ደህንነታችሁን ለመጠበቅ የሚረዳችሁ መንገድ የትኛው ነው?

ሀ. የጉዞ መንገዶችን ማወቅ

ለ. መንገድ ብቻችሁን አለማቋረጥ

ሐ. ስለ ደህንነት ከወላጆች ጋር መነጋገር

መ. ከላይ ያሉት ሁሉም መልስ ናቸው

4. ከሚከተሉት መካከል አንዱ የደህንነት መጠበቂያ ቅድመ ጥንቃቄ ነው?

ሀ. ከመጸዳጃ ቤት መልስ እጁን /ጇን አለመታጠብ

ለ. ማንኪያውን/ዋን ለሌሎች ማጋራት።።

ሐ. በሹል ወይም ስለታማ በሆኑ ቁሳቁሶች አለመጫወት።

መ. የሌሎችን ልጆች ደም መንካት ።

ምዕራፍ ሁለት

እውነትን እና ታማኝነት መሻት/ መፈለግ

ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

የእውነትን እና የታማኝነትን ትርጉም ትረዳላችሁ።

- የእውነት እና የታማኝነት ዓይነቶችን ትገልጻላችሁ ።
- የእውነተኛ እና የታማኝ ሰው ባህሪን ትለያላችሁ ።
- ለእውነት እና ለታማኝነት አስፈላጊነት ዋጋ ትሰጣላችሁ
- የእውነት እና የታማኝን ሰው ባህሪ ታሳያላችሁ።
- እውነት እና ታማኝነት አለመኖር የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ትለያላችሁ።

2.1 የእውነት እና የታማኝነት ትርጉም

የቀደመ ዕውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች፡-

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ሆናችሁ ተወያዩ እና መልሱን ለክፍሉ አጋሩ።

1. ለወላጆችህ እውነትን መናገር የሚኖርብህ ለምንድን ነው?
2. ለአስተማሪህ ታማኝ መሆን ያለብህ ለምንድን ነው?

እውነት ማለት እውነተኛ ወይም እርግጠኛ መሆን ማለት ነው። በሌላ በኩል ታማኝነት ማለት እውነትን ብቻ እና ከሥነ ምግባር አንጻር ትክክል የሆኑ ነገሮችን ማድረግ ወይም መናገር ማለት

ነው። ታማኝነት እውነትን መናገር ወይም አለመዋሸትን ይጨምራል። እውነት በሆነ መንገድ፣ እና ከሥነ ምግባር አንጻር ብቻ ትክክል የሆኑ ነገሮችን ማድረግ ነው። ለምሳሌ (አለመስረቅ ወይም አለመዋሸት ማለት ነው።)

2.2 የእውነት እና የታማኝነት ዓይነቶች

ተማሪዎች፣ የተለያዩ የእውነት እና የታማኝነት ዓይነቶች እንዳሉ መረዳት አለባችሁ። ዋናዎቹ ከዚህ በታች ቀርበዋል::

2.2.1 እውነትን መናገር

ስለ ታማኝነት ስታስብ "አትዋሽ" የሚለውን የግብረገብነት ምክር ታስታውሳለህ። ታማኝ መሆን ማለት ግን እውነትን ብቻ መናገር እና ማድረግ ማለት ነው። ለምሳሌ፣ እውነት ያልሆነውን ነገር መናገር ወይም ማውራት የታማኝነት ባህሪይ አይደለም።

ተገባር1፡

ከሚከተሉት ውስጥ እውነትን መናገሩን የሚያሳየው የትኛው ነው? መልሶቻችሁን ጥንድ ሆናችሁ ተወያዩ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሯቸው።

1. በቤትዎ ውስጥ ያለው ጠረጴዛ እንደሰበርክ አስብ: ከዚያም እናትህ ጠረጴዛውን የሰበረው ማን እንደሆነ እንድትነግራት ትጠይቅሃለች። ላንተ/ቺ እናት ስትመልስ/ሺ፡-

   ሀ/ ጠረጴዛውን አንተ/ቺ እንደሰበርክ/ሽ ትነግራትና ይቅርታ ትጠይቀለህ/ቂያለሽ።

   ለ/ ጠረጴዛውን የሰበረው ማን እንደሆነ እንደማታውቅ ትነግራታለህ/ሪያለሽ ።

2. በዮርዳኖስ ቤት እንድትሄድ እና እንድትጫወት እንደተፈቀደልህ አስብ፤ ይህን ግን አላደረክም። በምትኩ በመሐመድ ቤት ትጫወታለህ። ይሁን እንጂ አባትህ “ዛሬ በማን ቤት ተጫወትክ?” ብሎ ሲጠይቅህ።

   ከሚከተሉት ምላሾች ውስጥ የትኛውን ትመርጣለህ?

   ሀ. በዮርዳኖስ ቤት ተጫውችያለሁ ብለህ ትመልስለታለህ።

   ለ. በመሐመድ ቤት ተጫውችያለሁ ብለህ ትመልስለታለህ ።

   ሐ. በሁለቱም ቤት ተጫውችያለሁ ብለህ ትመልስለታለህ።

2.2.2 ቃልን መጠበቅ

መምህር ከበደ የ2ኛ ክፍል ቤተ-መምህር ናቸው። እናም ከ1ኛ እስከ 3ኛ ደረጃ ለሚወጡት ተማሪዎች በሴሚስተር መጨረሻ ላይ እስክብሪቶና መልመጃ ደብተር እንደሚሸልሚቸው ቃል ገብተዋል። በመጨረሻም መምህር ከበደ የገቡትን ቃል በመጠበቅ ለሶስቱ

ተማሪዎች የአንደኛ ወሰነ ትምህርት ማጠናቀቂያ ላይ ሽልማት አበርክተዋል።

ተግባር 2

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ቡድን ሆናችሁ ተወያዩ እና መልሶችሁን ለክፍሉ ተናገሩ

1. ከመምህር ከበደ ምን ተማራችሁ?
2. መምህር ከበደ እንዳደረጉት የገባኸውን ቃል መፈጸም አለብኝ ብለህ ታስባለህ? ለምን?

2.2.3 አትሰረቅ ወይም አትዋሸ

እውነት ስትደበቅ ችግር ውስጥ እንገባለን፣ ምክንያቱም ተግባራችን ልክ እንደ ውሸታም እና ሌባ ስለምንቆጠር ከሥነ ምግባር አኳያ ይህ ስህተት ነው ።

ተግባር 3፡

ከሚከተሉት ውስጥ ማጭበርበር ወይም መስረቅን የሚያሳየው የትኛው ነው? መልሶችህን በጥንድ ወይም በቡድን ተወያዩ እና ምላሾችህን ለክፍሉ ንገሯቸው።

1. እናትህ በኮምፒዩተር ላይ ጨዋታ እንድትጫወት ለ30 ደቂቃ ብቻ ፈቅዳለች፣እሷ ለአንተ ጊዜ /ቆጣሪ አዘጋጅታለች። በቀጣይ የምታደርገው የቱን ነው?

ሀ. ጨዋታውን በኮምፒዩተር ላይ መጫወት እንድችል በጊዜ /ቆጣሪ ላይ በድብቅ እጨምራለሁ።

ለ. ጊዜ ቆጣሪው ሲደወል የኮምፒተር ጨዋታ መጫወት አቆማለሁ።

2. አባትህ 10 ብር ሰጥቶህ ሙዝ በ7 ብር እንድትገዛ ፈቅዶልሃል፣ አንተ ግን ሙዙን በ5 ብር ብቻ ነው የገዛኸው። አባትህ ሙዙን በስንት ብር እንደገዛኸው ሲጠይቅህ ምን ትመልሳለህ?

ሀ/ ሙዙን በ7 ብር ገዛሁ ብዬ እመልስለታለሁ።

ለ/ሙዙን በ5 ብር ብቻ እንደገዛሁ እመልስለታለሁ።

2.3 የእውነተኛ እና ታማኝ ሰው ብቃት

ዮናታን ሁል ጊዜ እውነቱን ይናገራል ምክንያቱም ታማኝነት ከሁሉም በላይ አስፈላጊ ነው ብሎ ያምናል። አንዳንድ ልጆች በዮናታን ፊት መጥፎ ነገር ሲያደርጉ ማምለጥ እንደማይችሉ ያውቃሉ። ዮናታን መጥፎ ነገር ከሚያደርጉ ልጆች ጓደኝነት ይልቅ እውነትን መናገር አስፈላጊ ነው ብሎ ያምናል።

ተግባር 4፡

ከላይ ባለው ጽሑፍ ላይ በመመስረት ዮናታን ከዚህ በታች በተገለጹት ሁኔታዎች ውስጥ ምን ሊያደርግ እንደሚችል ተወያዩ።

መልሶችዎን በመልመጃ/ማስተወሻ ደብተር ላይ ይፃፉ።

1. አንድ ልጅ የዮናታንን እስክሪብቶ በጉልበት ወሰደ እና ዮናታን በእሱ ላይ ያደረገውን ለሌላ ሰው ቢናገር እንደሚጎዳው አስፈራራው። _____

2. የዮናታን የቅርብ ጓደኛ የሆነው ዘበርጋ ከትምህርት ቤት ቤተ መጻሕፍት መጽሐፍ ሰረቀ፣ ነገር ግን ዘበርጋ ስላደረገው ነገር ተጸጽቷል እና መጽሐፉን ወደ ትምህርት ቤቱ ቤተ መፃህፍት መለሰው። በተጨማሪም ዮናታን በቤተ-መጽሐፍት ባለሙያው ላይ ያደረገውን እንዳይናገር ጠየቀው። ዮናታን፡ _____

3. ዮናታን አዲሱን ፊልም እንዲያይ ወላጆቹ ስላልፈቀዱለት አፍሯል። ጓደኛው ዘበርጋ ዮናታን ስለፊልሙ መጨረሻ ምን እንደተሰማው ጠየቀው። ዮናታን፡_____

2.4 የእውነት እና ታማኝነት አስፈላጊነት

እውነት ተጨባጭ በሆነው ነገር ላይ ተመሥርቶ መናገርን ይጨምራል። ታማኝነት ስለምትናገሩት እና ስለምታደርጉት ነገር እውነትነት ያመለክታል። ታማኝነት በእኛ ግኑንነት እና ተግባር ይገለጻል። በመሆኑም እውነተኛ እና ታማኝ መሆን በሰዎች መካከል መተማመንን ይፈጥራል፣ የእርስ በርስ ግጭቶችን

ይቀንሳል፣ጓደኝነትን ያጠነክራል፣በወላጆቻችን እና በመምህራኖቻችን ተቀባይነትን ይጨምራል። ስለሆነም በህይወታችን እውነተኛ እና ታማኝ ሰው መሆን አስፈላጊ ነው።

ሃና

ሀሊማ ከዩኒቨርሲቲ ተመርቃለች። እሷ በጭራሽ አትዋሽም ፣ እናም እሷ ለራስዋም ለሌሎችም ታማኝ ናት። በአሁኑ ጊዜ አሠሪዎች እንደእሷ የሚሰሩ ሐቀኛ ሰዎች እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ። ሀሊማ ሐቀኛ በመሆኗ በአንድ ኩባንያ ውስጥ ጥሩ ሥራ አግኝታለች። ይህ ብቻ ሳይሆን ሀሊማ ታማኝ ስለሆነች ፈጣን እድገት አግኝታለች። በተጨማሪም ሀሊማ ለሥራዋ፣ ለአሰሪዎቿ ለሥራ ባልደረቦቿ እና ለደንበኞቿ ሐቀኛ ነች። ብዙ ጓደኞችም አሏት።

ተግባር 5፡ ከላይ ባለው ታሪክ ላይ ተመስርተው የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሱ መልሱን በማስተወሻ ወይም በመልመጃ ደብተር ላይ ፃፉ።

1. ሀሊማ ሐቀኛ ሴት ናት? ለምን?
2. ሀሊማ ለምን ጥሩ ስራ አገኘች?
3. ሀሊማ ብዙ ጓደኞች አሏት? ለምን?
4. እንደ ሀሊማ መሆን ትፈልጋለህ? ለምን?

5. እንደ ሀሊማ ሐቀኛ መሆን በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

ተማሪዎች ለእናንተ፣ ለአስተማሪዎቻችሁ እና ለወላጆቻችሁ ታማኝ መሆን አስፈላጊ ነው። ለአስተማሪዎቻችሁ እና ለወላጆቻችሁ ሁል ጊዜ ሐቀኛ ስትሆኑ ያምኑዋቹሃል። እንዲሁም ይወድዋችሃል። ወደፊት ስታድጉ እና በአካልም ሆነ በአእምሮ ጎልማሳ ስትሆኑ ወላጆቻችሁ እና አስተማሪዎቻችሁ ሁላችሁንም ሊቆጣጠሩዋችሁ እንደማይችሉ እውነት ነው። ነገር ግን ሁል ጊዜ ለወላጆቻችሁ እና አስተማሪዎቻችሁ ታማኝ ከሆናችሁ ስታድጉ እና የራሳችሁን ህይወት ስትኖሩ ደህንነታችሁን መጠበቅ እንደምትችሉ በተዘዋዋሪ ታረጋግጣላችሁ። ይህ ጽንሰ-ሐሳብ በአእምሮአችሁ ውስጥ ይዛችሁ የሚቀጥለው ተግባር ላይ በመመስረት አስተያየታችሁን ለጓደኞቻችሁ አካፍሉ::

ተግባር 6፡

የሚከተሉት ጥያቄዎች እውነትና ታማኝነትን የሚያመላክቱ ናቸው። በቡድን ተወያዩባቸው።


1.ትምህርት ቤታችሁ እንዳለ አስብ/ቢ እና ወደ መጸዳጃ ቤት ለመሄድ ፈቃድ እንዲሰጥህ/ሽ አስተማሪያችሁን ጠየቅ/ሽ። ከዚያም አስተማሪው እንድትሔድ/ጂ ፈቃድ ይሰጥሃል/ሻል፣ ነገር ግን ወደ እግር ኳስ ሜዳ ሄደህ/ሽ አስተማሪህ/ሽ በመጨረሻ እዚያ አገኘህ/ሽ?

2. እግር ኳስ እየተጫወትክ/ሽ እንደሆነ አድርገህ አስብ/ቢ እና በአጋጣሚ በቤትህ/ሽ የአትክልት ስፍራ የተገኘውን የአበባ ማስቀመጫ ሰበርክ። እንደ አለመታደል ሆኖ እናትህ ስትሰብር ትመለከትሃለች/ሽ። በኋላ የአበባ ማስቀመጫውን የሰበረው ማን ነው ብላ ትጠይቅሃለች። አንተ ግን ማን እንደሰበረው አላውቅም ትላታለህ/ትያታለሽ።

2.5 እውነተኛ እና ሐቀኛ የመሆን ጥቅም

ሀቀኛ ተማሪ በወላጆቹ፣ በጓደኞቹ እና በማኅበረሰቡ አባላት ይሸለማል፣ ይመሰገናል፣ ተቀባይነትም ይኖረዋል። እንዲሁም ይደነቃል። ስለዚህ “ታማኝነት ከሁሉ የተሻለው ነው” ማለት ይቻላል። ይህ ማለት ተማሪ ሁል ጊዜ ሐቀኛ መሆን አለበት ማለት ነው።

የታማኝ ሰው አጭር ታሪክ





ዋናተኛ መጥረቢያውን ፈልጎ ሲሰጠው

ታማኝነት

በአንድ ወቅት በአንዲት ትንሽ መንደር ውስጥ ይኖር የነበረ ከበደ የሚባል ሰው ነበር። ከበደ ድሃ ቢሆንም በጣም ቅን እና ታማኝ ሰው ነበር። ከመንደሩ ዳርቻ በተገኘች አንዲት ትንሽ ጎጆ ውስጥ ይኖር ነበር። ከበደ የብላቴ ወንዝ በማቋረጥ ወደ እርሻ ቦታ ይሄድ ነበር። አንድ ቀን መጥረቢያውን ይዞ ወንዙን እየተሻገረ ሳለ የብረት መጥረቢያው ከእጁ አምልጦ ወደ ወንዙ ውስጥ ወደቀ። በዚህም ምክንያት ከበደ በጣም ተጨነቀ። ከዚያም በወንዙ ዙሪያ ያለ አንድ ዋናተኛ መጥረቢያውን እንዲፈልግለት ጠየቀው። ቀጥሎም ዋናተኛው ጥያቄውን ተቀብሎ እጁን ወደ ወንዙ አስገባና የብር መጥረቢያ አውጥቶ ከበደ “ይህ መጥረቢያህ ነው?” ሲል ጠየቀው። ከበደ “አይ የኔ አይደለም ወንድሜ!” ሲል መለሰ። ከበደ የሚያስፈልገው የብረት መጥረቢያውን ብቻ ነው። ዋናተኛው ። እጁን ወደ ወንዙ ያስገባና የወርቅ መጥረቢያ አውጥቶ ከበደ የወርቅ መጥረቢያውን እንዲወስድ ነገረው። ይሁን እንጂ ከበደ ከዋናተኛው እጅ የወርቅ መጥረቢያውን ለመውሰድ ፈቃደኛ እንዳልሆነ ነገረው። መጨረሻም ዋናተኛው የብረት መጥረቢያውን ከወንዙ አውጥቶ ፈገግ ብሎ መጥረቢያውን ሰጠው። በመጨረሻም ከበደ እጅግ ተደስቶ ዋናተኛውን የብረት መጥረቢያውን ስላገኘለት አመስገነው። ዋናተኛውም ስለ ከበደ ታማኝነት በጣም ደስተኛ ሆነ። ስለዚህም

ብሩንና ወርቁን ምሳር ለከበደ ለታማኝነቱ ሽልማት ሰጠው። ከበደ እንደገና በጣም ደስተኛ ሆነ እና በደስታ ዘለሎ! ዋናተኛውንም ከልብ አመሰገነ።

ተግባር 7፡የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ በደብተራችሁ ላይ ፃፉ።

1. ከበደ ታማኝ ሰው ነው? ለምን?
2. ዋናተኛው ለከበደ ምን ሸለመው?
3. ከበደ የብርና የወርቅ መጥረቢያውን ከዋናተኛው ለመቀበል ያልፈቀደው ለምንድን ነው?
4. ዋናተኛው ለከበደ ፈገግታውን ያሳየው ለምንድ ነው?
5. ከበደ በጣም ደስተኛ የሆነው እና ዋናተኛውን ያመሰገነው ለምንድ ነው?
6.አንተ/አንቺ ከበደን ብትሆን/ኚ እሱ ያደረገውን ማድረግ ትችላለህ/ያለሽ? ለምን?

2.6 የእውነት እና የታማኝነት አለመኖር ውጤቶች

ይህን ሰው አትሁን!

በአንድ ወቅት ኃይሉ የሚባል የበግ መንጋ የሚጠብቅ እረኛ ነበር። አንድ ቀን ከመሰላቸት የተነሣ ለማታለል ወሰነና “እርዱኝ! ቀበሮ! እባካችሁ እርዱኝ!" ብዙም ሳይቆይ የመንደሮቹ ሰዎች ቀበሮን ለማባረር እና እረኛውን ከቀበሮው ለማዳን ዱላ ይዘው ወደ እሱ

ሮጡ። እረኛው ወዳለበት ሲደርሱ “ቀበሮው የት አለ?” ብለው በቁጣ ጠየቁት። እረኛው ግን ሳቀባቸውና እንዲህ ሲል መለሰላቸው፡- “ሁላችሁንም አሞኝኋችሁ! እዚህ ምንም ቀበሮ የለም” አለ።

ከዚያም የመንደሩ ሰዎች እረኛውን በንዴት ትተውት ሄዱ። ቢሆንም እረኛው ከስህተቱ መማር ስላልቻለ ያንኑ ተንኮል በመድገም የመንደሩን ሰው ብዙ ጊዜ ያታልላል። በዚህ ምክንያት የመንደሩ ሰዎች እረኛውን ማታለሉን እንዲያቆም ማስጠንቀቂያ ሰጡት። ከእለታት አንድ ቀን አንድ ቀበሮው እረኛው ኃይሉና በጎቹ ወደሚገኙበት የግጦሽ መስክ ገባና ቀስ በቀስ በጎቹን አንድ በአንድ ማጥቃት ጀመረ። ልክ እንደበፊቱ እረኛው በታላቅ ድምፅ “ቀበሮ! እርዱኝ እባካችሁ!”። የመንደሩ ነዋሪዎች የሱን ጩኸት ሰምተውታል ነገር ግን እንደለመደው ሊያታልለን ነው ብለው ስላሰቡ እሱን ለመርዳት ከቤታቸው አልወጡም ::
ኃይሉ ማንም ሊረዳው እንዳልመጣ ሲያውቅ ወደ መንደሩ እየሮጠ ሄዶ ቀበሮው በበጎች መንጋ ላይ ያደረገውን ለመንደሩ ነዋሪዎች ነገራቸው። ኃይሉ እያለቀሰ እንባውን ፣እያፋሰሰ “እርዳታ ጠራሁ! ለምን ግን ማንም ሊረዳኝ አልመጣም?" በመጨረሻም አንድ አዛውንት ግን ብልህ እና የተከበሩ የመንደር ነዋሪ “በጎቹ ላይ ስለደረሰው ነገር በጣም አዝነናል። ነገር ግን ውሸታም ሰው እውነት

ቢናገርም እንኳን ማንም ሰው እሱን እንደማያምን ማወቅ አለብህ አሉት።

ተግባር 8፡

ከላይ ባለው ታሪክ ላይ በመመስረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ እና መልሶቻችሁን በመልመጃ ደብተራችሁ ላይ ፃፉ።

1. ከላይ ካለው ታሪክ ምን ተማራችሁ?
2. እረኛው ከመንደርተኛው እርዳታ ማግኘት ያልቻለው ለምንድነው?
3. እረኛው ታማኝ ሰው ነው ብለው ያስባሉ? ለምን?
4. አስተዋዩ አዛውንት ለእረኛው ኃይሉ ከተናገረው ምን ተማራችሁ?
5. ታማኝነት ማጉደል ውጤቱ ምንድን ነው?

ምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ እውነት እና ታማኝነት ዓይነቶች፣ አስፈላጊነት፣ ሽልማት እንዲሁም የእውነት እና የታማኝነት አለመኖር የሚያስከተለው አሉታዊ ተጽዕኖችን ተምራችኋል ። ይህ ማለት እውነተኛ እና ታማኝ ሰው ሁል ጊዜ በሌሎች ሲታመን፡ ሐቀኝነት የጎደለው ሐሰት የሚናገር ሰው ደግሞ በሌሎች ዘንድ ፊጽሞ አይታመንም። ይህ የሚነግረን ሐቀኛ ያልሆኑና እና ሐሰተኛ ግለሰቦች ማግኘት የሚገባቸውን ነገሮች ማግኝት እንደማይችሉና እና ሥነ ምግባር የጎደለው ድርጊታቸው ቀስ በቀስ የማህበረሰቡን ሥነ-ምግባር እና ግብረ ገብነትን ሊሸረሸር እንደሚችል ነው።

ምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ ጥያቄዎች

I. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ 'እውነት' ትክክል ካልሆነ ደግሞ 'ሐሰት' ብላችሁ ጻፉ።

1. ሰዎችን እንዲያዙ በሚፈልጉት መንገድ መያዝ አለባችሁ።

2. ሰዎችን ከልብ ማዳመጥ አንዱ የስነምግባር መገለጫ ነው።

3. ለስህተቶቻችሁ ሁሉ ሌሎች ሰዎችን መውቀስ ተገቢ ነው።

4. ታማኝነት ማለት እውነተኛ መሆን እና እውነትን አለመደበቅ ማለት ነው።

5. አለመዋሸትህ የሚያሳየው ታማኝነትህን ነው።

II. ከዚህ በታች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጡ

1. ከሚከተሉት ውስጥ ፍትሃዊ አስተሳሰብ ያለው ሰው ባህሪ የትኛው ነው?

   ሀ. እሱ/ሷ ምክንያታዊ ነው/ናት።

   ለ. እሱ/እሷ ደንብን ያከብራል/ታከብራለች።

   ሐ.እሱ/እሷለሌሎችመልካም ነገሮችን ያበረክታል/ታበረክታለች።

   መ. ከላይ ያሉት ሁሉም መልስ ናቸው።

2. ታማኝነት የሚከተሉትን ያጠቃልላል።

   ሀ. እውነትን መናገር

   ለ. ከሥነ ምግባር አንጻር ትክክል የሆኑትን ብቻ ማድረግ

   ሐ. አለመስረቅ ወይም አለመዋሸት

   መ. ከላይ ያሉት ሁሉም መልስ ናቸው

3. የእውነት እና የታማኝነት መገለጫ ያልሆነው የትኛው ነው

   ሀ. እውነትን መናገር

   ለ. ቃል ኪዳንን መጠበቅ

   ሐ. መዋሸት

   መ. አለመስረቅ

4. ከሚከተሉት ውስጥ ታማኝ መሆን ያለብህ/ሽ ለማን ነው?

ሀ. ለወላጆች

ለ. ለመምህራን

ሐ. ለጓደኞች

መ. ሁሉም መልስ ናቸው

5. ከሚከተሉት ውስጥ የታማኝነት ጉድለት ውጤት የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. በወላጆችህ ዘንድ እምነት ማጣት።

ለ. ጓደኞችህ ካንተ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማቆም።

ሐ. በመምህራኖችህ መገለል ።

መ. ከላይ ያሉት ሁሉም መልስ ናቸው።

ምዕራፍ ሶስት

ፍትህ

ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ✓የፍትህ እና የፍትሃዊነት ጽንሰ-ሀሳብን ታብራራላችሁ፡፡
- ✓የፍትሃዊነትን አስፈላጊነት ዋጋ ትሰጣላችሁ፡፡
- ✓የፍትሃዊ አስተሳሰብን ባህሪ ታሳያላችሁ፡፡
- ✓በትምህርት ቤት እና በማህበረሰብ ውስጥ የሚፈጸሙ ኢ-ፍትሃዊ ድርጊቶችን መቃወም አስፈላጊ መሆኑን ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ የፍትህ አለመኖር የሚያስከትለውን ውጤት ትለያላችሁ፡፡

3.1 የፍትህ ትርጉም

ተማሪዎች ፍትህ ምን ይመስላችኋል? መልሳችሁን ለጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡ ፍትህ ማለት ሁሉንም ሰው ያለ ምንም አድልዎ በፍትሃዊነት መያዝ ማለት ነው፡፡ በብዙ አገሮች፣ አንዳንድ ታዋቂ ሰዎች ኢ-ፍትሐዊ ድርጊቶችንና አድሎአዊ ድርጊቶችን በመቃወም መርተዋል፡፡

- <u>ለምሳሌ</u> የኢትዮጵያው አቡነ ጴጥሮስ የጣሊያን ወራሪዎች በኢትዮጵያውያን ላይ ያደረሱትን በደልና መግዛት ተቃውመዋል።
- ደጅአዝማች ኡመር ሰሜተር የምዕራባውያንን ግፍ በመቃወም ለሀገሩ ኢትዮጵያ በሁለተኛው የኢጣሊያ-ኢትዮጵያ ጦርነት (1935-1941 እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር) ተዋግቷል።
- በደቡብ አፍሪካ አፓርታይድ ኔልሰን ማንዴላ በጥቁር ደቡብ አፍሪካውያን ላይ የሚደርሰውን የአፓርታይድ አድሎ እና ማግለልን ተቃውሞን መርቷል።
- ማርቲን ሉተር ኪንግ በአሜሪካ ውስጥ ለአፍሪካ-አሜሪካውያን ፍትሃዊ አያያዝና የማህበራዊ ንቅናቄን መርቷል።



አቡነጴጥሮስ



ደጅ አዝማች ኡመር ሰሜተር



ማርቲን ሉተር ኪንግ



ኒልሰን ማንዴላ

3.1. የፍትሃዊነት ጽንሰ-ሐሳብ

ፍትሃዊነት ማለት ሁሉም ሰዎች በቅንነት እና በአክብሮት ስኬታማ እንዲሆኑ እኩል እድል መስጠት፣ እርስ በርስ እንዲተባበሩ፣ ሁሉም ሰው ለልዩነቶች ዕውቅና እና ዋጋ መስጠት እንዲሁም ሌሎች ከዚህ በተለየ ሁኔታ እንዳይበደሉ ማድረግ ነው።

በአለም አቀፍ ደረጃ በፍትሀዊነት ከሚታወቁት እና በአርአያነት ከሚጠቀሱት ግለሰቦች መካከል እናት ቴሬዛ አንዷ ናቸው። ለሰው ልጅ ላላቸው የማይናቅ ፍቅር እና ርህራሄ አለም ሰላምታ ያቀርብላቸዋል። በጎሳ፣ በሀይማኖት፣ በቋንቋ እና በሌሎች ልዩነቶቻቸው ሳንለይ ፍቅራችንን እና ድጋፋችንን ለሚሹ ሰዎች እጃችንን እንዴት መዘርጋት እንዳለብን አስተምረውናል።



እናት ቴሬዛ

ተግባር 2፡ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ከተወያያችሁ በኋላ መልሶቻችሁን ለክፍሉ አጋሩ

1. በአካባቢያችሁ ውስጥ እንደ እናት ቴሬሳ ለሁሉም ሰዎች እኩል እድል የሚሰጥ እና ስኬታማ የሆኑ የምታውቋቸው ሰዎች አሉ? እነዚህ ሰዎች እነማን ናቸው ?
2. ከእናት ቴሬሳ ምን ተማራችሁ?

የፍትሃዊ ሰው ባህሪዎች

ፍትሃዊ ሰው የሚከተሉት ባህሪያት አሉት፡-

ፍትሃዊ ሰው ምክንያታዊ ነው። ይህ ማለት አንድ ሰው ግልጽ እና አስተዋይ አስተሳሰብ ሲኖር፤ አንድ መደምደሚያ ወይም ውሳኔ ላይ ከመድረሱ በፊት ሁለቱንም አዎንታዊ እና አሉታዊ ጎኖችን ሲመረምር፤ የፍትሃዊ ሰው አእምሮ ብሩህ መሆኑ ይህ ማለት

ታጋሽ፣ አድልዎ የሌለበት እና የሌሎችን አስተያየት የሚቀበሉ ናቸው።

በተጨማሪም የግልን አስተያየት በሌሎች ላይ አይጭኑም:: ፍትሃዊ ሰው ከአድሎአዊ አስተሳሰብ ነጻ ነው። ይህ ማለት የትምህርት፣ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ደረጃ ልዩነታቸውን ሳይለዩ ሁሉንም ሰዎች በእኩልነት ያስተናግዳሉ ።

ወይዘሮ መአዛ

ወይዘሮ መአዛ የሁለተኛ ክፍል የሂሳብ መምህርት ነች። ተማሪዎቿ በወላጆቻቸው የኢኮኖሚ ሁኔታ፣በእድሜያቸው፣ በጾታቸው፣ በፍላጎታቸው እና በችሎታቸው ይለያያሉ። ነገር ግን ወይዘሮ መአዛ ሁሌም ተማሪዎቿን ያለምንም አድሎ በክፍል ውስጥ በእኩልነት ታስተናግዳለች። ወይዘሮ መአዛ ሁሉንም ተማሪዎቿን ጥያቄዎችን ስትጠይቃቸው እኩል እድል ትሰጣለች። ሁሉንም ተማሪዎቿን ጥያቄዎችን በአግባቡ ሲመልሱ ታወድሳለች እንዲሁም ታበረታታለች።

ተግባር 3፡

ከላይ ያለውን ምንባብ መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያዩ።

1. ወይዘሮ መአዛ ፍትሃዊ አስተማሪ ናት? ለምን?

2. ወይዘሮ መአዛን ፍትሃዊ አስተማሪ እንድትሆን ያደረጋት ምንድን ነው?

3. ወይዘሮ መአዛ ባለብሩህ አእምሮ አስተማሪ ናት? ለምን?

3.2 የፍትሃዊነት አስፈላጊነት

ፍትሃዊነት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ በጣም አስፈላጊ ነው። ሁሉም ሰው፣ በእኩልነት፣ በመተሳሰብና በመረዳዳት እርስ በእርሳቸው ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ሲስተናገዱ መተማመንን ሊያዳብሩ ይችላሉ።

ተግባር 4፡

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ሆናችሁ ተወያዩና መልሶቻችሁን ለክፍሉ አጋሩ

1. አንድ ነገር ፍትሃዊ እንዳልሆነ እንዴት ማወቅ ይቻላል?
2. ሰው አታልሎህ/ሽ ወይም ዋሽቶህ/ሽ ያውቃል? ሲያታልልህ/ሽ ወይም ሲዋሽህ/ሽ ምን ተሰማህ/ሽ?

የትምህርት ቤት ጓደኞች

በቀለች፣ ፋጡማ እና ራሄል የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። ብዙን ጊዜ በምሳ ሰዓት አብረው ጨዋታ ይጫወታሉ። ሁልጊዜ ጨዋታቸውን የሚጫወቱት በጨዋታው ህግ መሰረት ነው። ነገር ግን በቀለች፣ ፋጡማን እና ራሄልን በማታለል ሁለት ጊዜ

ተጫውታለች። የምትጫወትበትን ተራዋን አልጠበቀችም። በዚህ ምክንያት ራሄል ከበቀለች ጋር መጫወት አቆመች። ራሄል በቀለች እንዴት እንዳታለለቻቸው ለፋጡማ ስትነግራት እሷም ተናደደች። በመጨረሻም ሁለቱም እሷን ማመን ስላቃታቸው ከበቀለች ጋር የተመደቡባቸውን ስራዎች እና ማንበባቸውን አቆሙ።

ተግባር 5: ከዚህ በላይ ባለው ጽሁፍ ላይ በመመስረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያዩ እና መልሳችሁን በመልመጃ ደብተራችሁ ላይ ጻፉ ።

1. ፋጡማ እና ራሄል በበቀለች ላይ የተናደዱት ለምንድን ነው?
2. ፋጡማ እና ራሄል ምድባቸውን የተመደቡባቸውን ስራዎች ለመስራት እና ከበቀለች ጋር ማንበብ ለምን አቆሙ?
3. በቀለችን ብትሆን ምን ታደርጋለህ?
4. በቀለች ለምን የጨዋታውን ህግ አልተከተለችም?
5. ፋጡማ እና ራሄል ለበቀለች ፍትሃዊ ናቸው ብለህ ታስባለህ? ለምን?

3.3 ፍትሃዊ አስተሳሰብ ያለው ሰው ባህሪያት

የቀደመ ዕውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

በቡድን ሆናችሁ የሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ

1. ፍትሃዊ እና ነጻ አስተሳሰብ አስፈላጊ ነው? ለምን? ነጻ አስተሳሰብ አስፈላጊ ነው ምክንያቱም በጉዳዮቻችን ላይ ያሉን

አብዛኛዎቹ አመለካከቶቻችን እና እምነቶች ምክንያታዊ ላይሆኑ ይችላሉ እና ሌሎች በሚሰጡን የግል አስተያየቶች ሊነኩ ይችላሉ።

ፍትሃዊ- አሳቢዋ ፌበን

ሀዋ፣ ናቲ እና ፌቤን የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። ሃዋ ስለ አስተሳሰቧ ደንታ የላትም። እንደወደደችው ማድረግ ያለባትን ታደርጋለች። በሌላ በኩል ናቲ በአስተሳሰብ ጎበዝ ነው ነገር ግን ለሌሎች ፍትሃዊ አይደለም። ናቲ ሁሉንም ነገሮች ብቻውን ማድረግ የሚፈልግና የሌሎችንም ሀሳብ የማይቀበልና ሃሳቡን እና ቁሳቁሶቹን በጭራሽ ለሌሎች ለማካፈል ፍቃደኛ አይደለም። ይሁን እንጂ ፌበን በአስተሳሰብ ጎበዝና ለሌሎች ፍትሃዊ ነች። የግል ታማኝነት እና እምነትን ከመጉዳት ይልቅ የማዳበር ችሎታ ያላት፣ የሰዎችን ሀሳብ የምትቀበል እና ያላትን ሀሳብና ቁሳቁስ እኩል የምታካፍልና የማታዳላ ናት።

ተግባር 6፡ ከላይ ባለው ጽሁፍ ላይ በመመስረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያዩበት እና መልሱን በደብተራችሁ ላይ ፃፉ።

1. ከሦስቱ መካከል የፍትሃዊነት አስተሳሰብ ባህሪ ያለው ማን ነው?
2. ፌቤን ለጓደኛዋ ፍትሃዊ ናት? ለምን?
3. ናቲ ለጓደኛው ፍትሃዊ ነው? ለምን?

4. ከሦስቱ ተማሪዎች የማንን ባሕርይ ይወዳሉ? ለምን?

3.4 የፍትህ መጓደል የሚያስከትለው ዉጤት

በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ፍትሃዊነት ከሌለ ምን እንደሚፈጠር አስሱ። በእንደዚህ ዓይነት አውድ ውስጥ ሲኖር በሰዎች ዘንድ አለመስማማት፣ እርስ በርስ መጣላት፣ ሰዎች በጋራ አብረው አለመስራ እንዲሁም በእንደዚህ አይነት አከባቢ ለመኖር ፍላጎት የማጣት የመሳሰሉትን ያስከትላል። ይሁን እንጂ ሰዎች ፍትሃዊነት በሚስተናገዱበት ማህበረሰብ ውስጥ ሁሉም ሰው አብሮና ተባብሮ ይሰራል፣ ችግሮችን በቀላሉ ይፈታል፣ ይዝናናል፣ አንዱ ከሌላው ጋር ይተሳሰባል፣ ፍጹም ደህንነት ይሰማቸዋል እናም ረጅም እድሜ ይኖራል። ይህ ብዙ ሰዎች በእርግጠኝነት መኖር የሚፈልጉት ህይወት ነው።

ርዕሰ መምህር ዶጊሶ

አቶ ዶጊሶ የመንግስት ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ናቸው። የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች እና መምህራን ወጥ በሆነ መልኩ የትምህርት ቤቱን ህግ አይከተሉም። ለምሳሌ አንዳንድ ተማሪዎች የደንብ ልብሳቸውን ሳይለብሱ እና አርፍደው ወደ ትምህርት ቤቱ ይመጣሉ። በተጨማሪም አንዳንድ መምህራኖች ወደ ክፍል ውስጥ ሲገቡ የደንብ ልብሳቸውን ይለብሳሉ፣ አንዳንዶቹ ግን ይህን

አያደርጉም። ይሁንና አንዳንድ ተማሪዎች እና መምህራን ደንቡን የማይከተሉትን እንደ አርአያ ይቆጥሯቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ መምህራን አይተባበሩም፣ ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር እና በአንዳንድ መምህራን ኢ-ፍትሃዊ ድርጊት እንደተፈጸመባቸው ያስባሉ:: ይህ ሁኔታ ተማሪዎቹን እርስ በእርሳቸው እንዳይተባበሩ፣ ችግሮችን የመፍታት ክህሎታቸው አናሳ እና ስለ ሌሎች ስሜት እና ደህንነት እንዳይጨነቁ አድርጓቸዋል::

ተግባር 7፡ ከላይ ባለው ጽሑፍ ላይ በመመስረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያዩ።

1. ሌሎች ተማሪዎች በትምህርት ቤት የደንብ ልብሳቸውን ከለበሱት ጋር መቀላቀል የሚፈልጉት ለምንድን ነው?
2. ተማሪዎቹ በዳይሬክተሩና በትምህርት ቤቱ አንዳንድ መምህራን ፍትሃዊ እንዳልሆኑ የሚሰማቸው ለምንድን ነው?
3. በትምህርት ቤቱ ውስጥ መምህራን የማይተባበሩት ለምንድን ነው?
4. ትምህርት ቤቱ አንድ ወጥ የሆነ ደንብ አለመኖሩ በተማሪዎቹ ላይ ምን ፈጠረ?

3.5 ለፍትህ መቆም

ለፍትህ የግለሰብ አቋም መውሰድ

የህግ የበላይነትን ማክበር እና ማስከበር ለፍትህ መቆም የመጀመሪያ እርምጃ ነው። ይህ ከባድ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን በተቻለ መጠን ኢ-ፍትሃዊ ናቸው ብላችሁ በምታስቧቸው ነገሮች ላይ ድጋፋዊ አስተዋፅዖ አለማድረግና በራሳችሁ ባህሪ ውስጥ ፍትሃዊ ለመሆን መሞከር ያስፈልጋል።

ተግባር 8፡ ከዚህ በታች ያለውን ታሪክ አንብቡ እና የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያዩ።

የክፍል ጓደኞች

ኪባሞ እና ሎኢቱ የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። አንድ ቀን ኪባሞ በቤቱ እርሳሱን ረስቶ ወደ ትምህርት ቤት መጣ። ከዚያም የሒሳብ መምህራቸው ወደ ክፍል ሲገባ እርሳሱ የራሱ እንደሆነ በማስመሰል ወዲያውኑ የሎኢቱን እርሳስ ወሰደ። አለሙ ኪባሞን ከሎኢቱ ከረጢት ውስጥ እርሳሱን ሲወስድ ምንም እንኳን አለሙ እና ኪባሞ ጓደኞሞች እና ጎረቤታሞች ቢሆኑም ያየዋል።

አለሙ እርሳሷን ኪባሞ እንደወሰደ ለመምህሩ ነገረው። ኪባሞ ተግባሩን ሙሉ በሙሉ ካደ እና ለመምህሩ “ይህ እርሳስ የእኔ ነው”

ሲል መለሰ። ይሁን እንጂ መምህሩ ነገሩ ስለገባው ኪባሞን እርሳሱን ለሎኢቱ እንዲመልስ አደረገው።

1. ከኪባሞ ተግባር ምን ይማራሉ?

2. ከመምህሩ ተግባር ምን ተማራችሁ?

3. ከአለሙ ተገባር ምን ተማራችሁ?

4. አንተ/ቺ አለሙ ብትሆን/ኚ ምን ታደርጋለህ/ታደርጊያለሽ?

5. ኪባሞ ጓደኛህ/ሽ ቢሆን ትደግፋለህ/ትደግፊያለሽ? ለምን?

ተግባር 9፡ ከዚህ በታች ያለውን ታሪክ አንብቡ እና በእሱ ላይ ተመስርተው የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

አንድ ቀን አቶ ሴታ በአንድ ክፍል ውስጥ ከነበሩት አጠቃላይ ተማሪዎች በ5 ያነሰ ከረሜላ የያዘ የፖስታ ቦርሳ አመጡ። የፖስታ ቦርሳውን በክፍል ውስጥ አከፋፈል እና ለእያንዳንዱ ተማሪ እያንዳንዳቸው አንድ ከረሜላ መውሰድ እንደሚችሉ ነገራቸው። በመጨረሻም ከረሜላ ያላገኙት ተማሪዎች ለሁሉም ሰው የሚሆን በቂ ከረሜላ እንደሌለ አወቁ እናም ውድቅ እና ኢ-ፍትሃዊ አያያዝ ተሰምቷቸዋል።

1. ከረሜላ ያላገኙት ተማሪዎች ምን ተሰማቸው?
2. ለችግሩ ትክክለኛ መፍትሄ ምንድን ነው ትላላችሁ?
3. ሰዎች በደል ሲደርስባቸው ውድቅ እንደሚያደርጉ የሚሰማቸውን ተመሳሳይ ሁኔታ አስብ?

የምዕራፍ ሶስት ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ ፍታዊነት ትርጉም ፣ የፍትህ ዓይነቶች ፣ የፍትሃዊነት አስፈላጊነት ፣ የፍትሃዊ አስተሳሰብ ባህሪ ፣ ውጤቶቹ እና የፍትህ አለመኖር እና ለፍትሕ መጓደል መቆምን ተምረዋል ። ይህን በማድረጋችሁ ፍትህ ለሰው ልጅ በሰላም አብሮ ለመኖር በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ተምራችኋል። ፍትሃዊ እና ፍትሃዊ አስተሳሰብ ለማህበረሰቡ ጠቃሚ መሆኑንም ተምራችኋል ምክንያቱም ፍትሃዊነት ሲጠፋ በህዝቡ መካከል ግጭት ይፈጠራል። ስለዚህ ብቻችሁንም እንኳ ብትሆኑ ለፍትህ መቆም አለባችሁ።

የምዕራፍ ሶስት ማጠቃለያ ጥያቄዎች

I. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ 'እውነት' ትክክል ካልሆነ ደግሞ 'ሐሰት' ብላችሁ ጻፉ።

1. ለፍትህ የቆመ ሰው ሊመሰገን ይገባዋል።
2. ፍትሃዊነት ማለት ሁሉንም ሰው በቅንነት እና በአክብሮት መያዝ ማለት ነው።
3. ፍትሃዊነት ለራስ ብቻ አስፈላጊ ነው።
4. ለራስህ ስትል ብቻ ህግን ማክበር ለፍትህ እንደመቆም ይቆጠራል።
5. ፍትሃዊ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ከራሳቸው ጉዳይ ይልቅ በሌሎች ሰዎች ጉዳይ ላይ ትኩረት ይሰጣሉ::

II. ከዚህ በታች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጡ

1. ከሚከተሉት ውስጥ የፍትሃዊ ሰው ባህሪ የትኛው ነው?

   ሀ. ፍትሃዊ ሰው ምክንያታዊ ነው።

   ለ. ፍትሃዊ ሰው ሌሎችን ለመረዳት ሁሌም ዝግጁ ነው።

   ሐ. ፍትሃዊ ሰው አያዳላም

   መ. ከላይ ያሉት ሁሉም መልስ ናቸው

2. ፍትሃዊ በሰፈነበት ማህበረሰብ ውስጥ ሰዎች፡-

ሀ. እርስ በርሳቸው ይከባበራሉ፡፡

ለ. ደህንነት ይሰማቸዋል፡፡

ሐ. በፍቅር አብሮ ስራዎችን ይሰራሉ፡፡

መ. ከላይ ያሉት ሁሉም መልስ ናቸው

3. ከሚከተሉት ውስጥ የፍትሃዊ አስተሳሰብ ባህሪ ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ሌሎችን ለመረዳት ዝግጁ መሆን

ለ. ምክንያታዊ መሆን

ሐ. ኢ-ምክኒያታዊ መሆን

መ. እጅ በእጅ መስጠት

4. ፍትሕ ከሌለ በማኅበረሰባችሁ ውስጥ ምን ሊፈጠር ይችላል?

ሀ. ሁሉም ሰው እርስ በርስ ይተማመናል

ለ. ሰዎች አብረው ስራዎችን ያለመስራት

ሐ. ሰዎች በቀላሉ ችግሮችን መፍታት ይችላሉ

መ. ከላይ ያሉት ሁሉም መልሰ ናቸው፡፡

5. ለፍትህ መቆም ማህበረሰቡን ለምን ይረዳል፡-

ሀ. አንዱ ከሌላው ጋር ለመተባበር

ለ. ፍትሃዊነትን ለማበረታታት

ሐ. እርስ በርስ ለመተማመን

መ. ከላይ ያሉት ሁሉም መልስ ናቸው።።

ምዕራፍ አራት

አምንታዊ ማህበራዊ መስተጋብር

ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- አምንታዊ ማህበራዊ መስተጋብር ምን ማለት እንደሆነ ታብራራላችሁ፡፡
- በትምህርት ቤት እና በማህበረሰብ ውስጥ ያሉ የማህበራዊ ግንኙነቶችን የማስተዋወቂያ መንገዶችን ታውቃላችሁ፡፡
- የአምንታዊ ማህበራዊ ግንኙነት ጠቀሜታ አስፈላጊነትን ትለያላችሁ፡፡
- የአምንታዊ ማህበራዊ መስተጋብር ችግሮችን ትለያላችሁ፡፡
- በመካከላችሁ አምንታዊ የአቻ ማህበራዊ ግንኙነቶችን ታሳያላችሁ፡፡

4.1 አምንታዊ ማህበራዊ ግንኙነት ትርጉም

የቀደመ ዕውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

ውድ ተማሪዎች በትምህርት ቤትህ ውስጥ የቅርብ ጓደኛ አላችሁ?
ወዳጅነታችሁ የቅርብ ወዳጅነት እንዲሆን ምን አደረጋችሁ?
ጓደኛ የማግኘት ጥቅሞች ምንድን ናቸው?

ሰው እንደመሆናችን መጠን ሁላችንም እንደ ወላጆቻችን፣ እህቶቻችን፣ ወንድሞቻችን፣ እና ጎረቤቶቻችን እንዲሁም በትምህርት ቤት ከክፍል ጓደኞቻችን ጋር ማህበራዊ ግንኙነት ለመመስረት ሁላችንም ፍላጎት አለን። በመልካም ጓደኝነት የሚታወቅ እና በግንኙነት ላይ የተሰማሩትን ፍላጎት የማያበላሽ ማህበራዊ ግንኙነት አዎንታዊ ማኅበራዊ መስተጋብር ይባላል።



ተማሪዎች ከክፍል ውጪ ባሉ መጫወቻዎች አንድ ላይ ሲጫወቱ



ልጆች እና ወላጆች መካነ እንስሳትን ሲጎበኙ

ተግባር 1፡ በመጀመሪያ ከላይ በተጠቀሰው አንቀጽ እና ስዕላዊ መግለጫ ላይ በመመስረት የማህበራዊ ግንኙነት ጥቅሞችን በወረቀት ላይ በግል ይፃፉ። ከዚያ ዝርዝሮችዎን ከእኩያዎቻችሁ ጋር ተለዋወጡ እና መልሶቻችሁን አነፃፅሩ።

ሳራ እና ሀሊማ አዲስ ጓደኝነት እየጀመሩ ነው



ሳራ እና ሀሊማ ተግባብተው ሰላምታ ሲለዋወጡ

ሳራ፡ ደህና አደርሽ ሀሊማ?

ሀሊማ፡ ደህና አደርሽ ሳራ

ሳራ፡- በክፍላችን ውስጥ የቅርብ ጓደኛ የለኝም። የቅርብ ጓደኛዬ ለመሆን ፈቃደኛ ነሽ?

ሃሊማ፡ ወይ ሳራ እኔም እኮ የቅርብ ጓደኛ የለኝም፣ እናም ጥያቄሽን በደስታ ተቀብያለሁ። ግን ጥሩ ጓደኛ ለመሆን ብቁ እንደሆንኩ ልትነግሪኝ ትችያለሽ?

ሳራ፡ ሀሊማ አመሰግናለሁ። እኔ እንደማስበው ጥሩ ጓደኛ የምለው የጋራ ፍላጎት፣ ትርፍ ጊዜን በጋራ የማሳለፍ ፍላጎት ያላት፣ ተገቢውን ቁሳቁስ በጋራ የምታካፍለዋን ነው። በነገራችን ላይ ካንች ጋር ስጫወት ምቾት ይሰማኛል። ሀሊማ አንቺም የምትፈልጊውን የጥሩ ጓደኛ ባህሪን ንገሪኝ?

ሀሊማ፡- አዎ ሳራ። ምርጫሽን ስለነገርሽኝ አመሰግናለሁ። ከተናገርሺው በተጨማሪ እሷም ጓደኛዋን መንከባከብ እንዳለባት እፈልጋለሁ።

ሳራ: ዋው ሃሊማ ድንቅ ነሽ! ለአንቺ እና ለሌሎች እንደዚህ አይነት ጓደኛ ለመሆን የተቻለኝን ሁሉ እሞክራለሁ።

ሀሊማ፡ አመሰግናለሁ ሳራ።

ሳራ፡ እኔም አመሰግናለሁ።

ከላይ ባለው ሰላምታ ልውውጥ ላይ እንዳነበባችሁት ሳራ እና ሃሊማ የመልካም ጓደኝነትን ባህሪያቶች ገልጸውላቸዋል።


ተግባር 2፡ ከላይ በተጠቀሰው ውይይት ላይ በመመስረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጥንድ መልሱ፡

1. የጥሩ ጓደኝነት ባህሪያት ምንድን ናቸው?

2. ጥሩ ጓደኛ ሊያደርጉህ የሚችሉ መልካም ባህሪያት ምንድን ናቸው?

ማህበራ ክህሎቶች/ ችሎታዎች

ማህበራዊ ክህሎቶች መልካም እና ጤናማ ግንኙነት ለመመስረት እና ግንኙነቶችን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ተገቢ ባህሪያቶች እና ተግባራት ናቸው። አዎንታዊ ውጤት በሚያስገኝ መንገድ ከሌሎች ጋር እንድትገናኝ የሚረዱ ችሎታዎች ናቸው። እነዚህም ሰላምታ መለዋወጥ፣ አቀባበል፣ ትብብር፣ ማጋራት እና ሌሎች ችግር ውስጥ ያሉትን መርዳትን ያካትታሉ።



የክፍል ጓደኞሞች ትናንሽ ካርቶኖችን ለመደርደር ሲተባበሩ ።



ተማሪዋ የጓደኞዋን ዊልቸር በመግፋት ስትረዳው

ተግባር፡3

ከለይ ካለው ሥዕላዊ መግለጫ ምን ተረዳችሁ ወይም ተማራችሁ?

በማህበራዊ ግንኙነት መተባበር በጣም አስፈላጊ እሴት መሆኑን ማወቅ አስፈላጊ ነው። እውነት ነው የተለያዩ ሰዎች የተለያዩ የግንኙነት ክህሎት እና ችሎታ ወይም ስጦታ አላቸው። ስለዚህ ሲተባበሩ ለጋራ ዓላማ ስኬት አስተዋፅዖ ያደርጋሉ። መተባበር ማህበራዊ ግንኙነት ላይ ካሉት መሠረታዊ ነገሮች ውስጥ አንዱ ነውና ለአንድነት መሰረትን ይጥላል። አንድነት ጥንካሬን ሲያመጣ መከፋፈል ግን ውድቀትን ያመጣል።

ተከታዩ ታሪክ ይህንን እውነታ ያስረዳል። ሦስቱ ወንዶች ልጆች እና እስር ትናንሽ እንጨቶች ወይም አርጩሜዎች

በአንድ ወቅት አንድ አዛውንት ከሶስት ልጆቹ ጋር በአንድ የገጠር መንደር ውስጥ ይኖሩ ነበር። ሁሉም ወንድማማቾች ታታሪ ሠራተኞች ቢሆኑም አብረው መሥራትን ግን አይወዱም። ሁልጊዜ ይጨቃጨቁ ነበር። ይሁን እንጂ አባታቸው እነሱን አንድ ለማድረግ ብዙ ጥረት አድርጓል ነገር ግን አንድ ማድረግ አልቻሉም ።

አዛውንቱ ታምመው ሳለ ወንድማማቾቹ አንድ እንዲሆኑ የተሰጣቸውን ምክር ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው

ልዩነታቸውን ረስተው አንድ ሆነው እንዲቆዩ አንድ ተግባራዊ ትምህርት ሊሰጧቸው ፈለጉ።

እናም ልጆቹን ጠሯቸው ለእያንዳንዳቸው አስር ትናንሽ እስር አርጬሜዎችን ሰጧቸው እና እያንዳንዱን ትናንሽ አርጬሜዎችን እንዲለዩ አዘዛቸው። ከዚያም እያንዳንዱን ትናንሽ አርጬሜዎችን በፍጥነት ለሰባበረ ልጅ ሽልማት እንደሚሰጡ ቃል ገቡ። ሁሉም በደቂቃዎች ውስጥ ቁራጮችን ወደ ቁርጥራጮች ቀየሩ። ዳግመኛም ማን ቀድሞ ጨረሰ ብለው ተከራከሩ።

አባትየውም፣ "ልጆቼ፣ አትጨቃጨቁ ጨዋታው አላለቀም። ለእያንዳንዳችሁ ሌላ የጥቅል አርጬሜዎችን እሰጣችኋለሁ እናም በጥቅል መሰባበር እንጂ በተለይ አርጬሜዎች መሰባበር አይቻልም አሉ" ነገር ግን ሁሉም ልጆች የቻሉትን ቢሞክሩም ሁሉም መስበር አልቻሉም።

በመጨረሻም አባትየው፣ "ውድ ልጆቼ፣ ተጠንቀቁ! በተናጠል ስሆን በቀላሉ ተሰብረዋል። ይህ የሚያሳየው አንድ ከሆናችሁ ማንም ሊጎዳችሁ እንደማይችል ነው። ነገር ግን ሁላችሁም ብትነታረኩ ማንም ሰው በቀላሉ ሊያበሳጫችሁ እና ሊያሸንፋችሁ ይችላል። ስለዚህ በአንድነታችሁ እንድትቆዩ እመክራችኋለሁ። በመጨረሻም

ሦስቱ ልጆች የአንድነቱን ኃይል ተረድተው ለአባታቸው በአንድነት እንደሚቆዩ ቃል ገቡ።

ተግባር4፡

ከላይ ካለው ታሪክ ምን ተማራችሁ?

የሚከተሉት ለአምንታዊ ማህበራዊ ግንኙነቶች ጠቃሚ የሆኑ የማህበራዊ ክህሎቶች ምሳሌዎች ናቸው።

የማህበራዊ ክህሎቶችና ምክሮች	እንዴት እንደሚናገሩ ምሳሌ፣
የጨዋታ ሀሳቦችን ማነሳሳት	ምስራቅ፣ ወደ መካነ እንስሳት እንሂድ።
የአቻዎችን ግብዣ ተቀበል	እሺ ከማል ፣ እኔ እቀላቀላችኋለሁ።
የጓደኛን ትኩረት ማግኘት	አዜብ፣እስቲ አንድ እንቆቅልሽ እንስራ
ዕቃዎችን ማጋራት	አለሚቱ፣ የእኔ ተጨማሪ ቀለሞች እዚህ አሉ። እነሱን መጠቀም ይችላሉ።
ዕቃዎችን እንዲያካፍል ጓደኛን በመጠየቅ	ሙሴ፣ ማጥፊያህን መዋስ እችላለሁ እባክህ?
ለጓደኛ ጥሩ ነገር መናገር	ፎዚያ፣ መልካም ቀን ይሁንልሽ

ጓደኛ አመሰግናለሁ	አኔም አመሰግናለሁ አደንቃለሁ
ጨዋነት	ሸንት ቤት መሔድ እችላለሁ?

በተቃራኒው እነዚህ ችሎታ የሌላቸው ተማሪዎች ግንኙነታቸውን የሚጎዱ ተቀባይነት የሌላቸው ባህሪያትን ሊያሳዩ ይችላሉ። የእንደዚህ አይነት አሉታዊ ተግባራት ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡- ጓደኛን መግፋት ወይም መምታት እና ከእነሱ ጋር ለመነጋገር የሚሞክርን ጓደኛ አለመቀበልና የመሳሰሉት ናቸው። ስለዚህ ከእንደዚህ አይነት ድርጊቶች መራቅ እና እንደ ትብብር፣ ይቅርባይነት፣ ልግስና እና መረዳዳት ያሉ ጥሩ ግንኙነቶችን ሊያዳብር የሚችል መልካም ልማድ ማዳበር አስፈላጊ ነው። በእርግጥም ለሌሎች መልካም ማድረግ ምንጊዜም ጠቃሚ ነው። አዎንታዊ ግንኙነት በመስጠት እና በመቀበል መርህ ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት።

ተግባር 5፡ ከላይ በተጠቀሱት የማህበራዊ ክህሎቶች ምሳሌዎች ላይ በመመስረት ቡድን ፈጥራችሁ በማህበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ የራሳችሁን ተቀባይነት ያላቸው እና የሌላቸው ባህሪያትን ዘርዝሩ።

4.2 ጠቃሚ አዎንታዊ መንገዶች እና ማህበራዊ ግንኙነቶች

ከጓደኞችና ከሌሎች ሰዎች ጋር በተለያዩ ጉዳዮች መልካም ግንኙነት ለማድረግ የሚረዱ ስልቶችና መንገዶች የሚከተሉ ናቸው። የመጀመሪያው ስልት የቃል ያልሆኑ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም የአይን ንክኪ መፍጠር፣ ማራኪ ድርጊት እና የወዳጅነት ምልክት በማሳየት የግንኙነት እና የመቀራረብ ክህሎትን ማዳበር ነው። እንደዚህ አይነት ተገቢና የቃል ያልሆኑ መግባቢያዎች ለእሱ/ሷ ፍላጎት እንዳለህ እኩዮችህ እንዲያውቁ ያደርጋል።

ሁለተኛው ስትራቴጂ አንተና እና እኩያህ ስለራሳችሁና ስለሌሎች በዝርዝር እንዲተዋወቁ እድል የሚሰጥና በሁለት በኩል ትክክለኛ የመረጃ ልውውጥ ማድረግ ነው። ለምሳሌ ስለስምህ፣ እድሜህ፣ ሰፈርህ፣ የምትወዳቸውን እና የማትወዳቸውን እንዲሁም ስለ ፍላጎትህ መረጃ መለዋወጥ ትችላለህ። (ለምሳሌ “ሠላም ስሜ እርስቱ ነው። ስምህ ማን ነው?”)

ተግባር 6፡

በክፍል ውስጥ ሁለት በጎ ፈቃደኞች የሆኑ ተማሪዎች የሚትወዱትና የማትወዱትን የመልካም ጓድኝነት ጨዋታ ተጫወቱ። የእርስ በርስ ዝርዝር ዕውቀት እና ግልጽነት ረጅም ጊዜ

የሚቆይ እና በጋራ የሚጠቅም ጓደኝነትን ለመገንባት ያግዛሉ። ነገር ግን የተደበቀ ፍላጎት ጓደኝነትን ሊጎዳ ይችላል።

ሦስተኛው ስልት በአንተ እና በእኩያህ/ሽ ወይም በጓደኛ መካከል ያለውን ተመሳሳይነት እና ልዩነት በግልፅ መለየት ነው። አራተኛው ስልት በቡድን ውስጥ በጋራ የመሥራት ክህሎትን ማዳበር ነው።

4.3 የመልካም ማህበራዊ ግንኙነት አስፈላጊነት

ከላይ ባለው ሀሳቦች ውስጥ፣ ግንኙነትን እና ጓደኝነትን ለመመስረት አስፈላጊ የሆኑትን ማህበራዊ ክህሎቶች እና ተገቢ ማህበራዊ ግንኙነቶችን ለማስተዋወቅ የሚረዱ ስልቶችን ተምራችኋል። በዚህ ትምህርት ውስጥ ስለመልካም ማህበራዊ ግንኙነት አስፈላጊነት ትማራላችሁ። ከሌሎች ሰዎች ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲኖረን ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው ምክንያቱም ጥሩ ስሜት እንዲሰማን ስለሚያደርግ እና ከሌሎች ጋር ስንነጋገር፣ ስንጫወት እና ሃሳባችንን ለሌላ ሰው ስናካፍል ብቸኝነት እንዳይሰማን ያደርገናል። መልካም ጓደኝነት ታማኝነት፣ ልግስና፣ ሰብአዊነት፣ ይቅርታ እና መስዋዕትነት ይፈልጋል ። እነዚህ ብቃቶች በመልካም ማህበራዊ ግንኙቶች መሳተፍ ለሚፈልጉ በጣም የሚጠቀሙ ናቸው። እነዚህ በጓደኝነት ህይወት ውስጥ ችግሮችን ለመፍታት ይረዳሉ። ከዚህም በላይ በጓደኝነት ውስጥ እርስ በርስ

የተለያዩ ማህበራዊ ክህሎቶችን፣ እውቀትን እና የግብረ ገብ እሴቶችን እንማራለን።

ተግባር 7፡ ከላይ ባለው ጽሁፍ ላይ በተገለፀው መልካም ማህበራዊ ግንኙነት ጥቅሞች ላይ ተወያዩ። የየራሳችሁን ሁለት የመልካም እና የማህበራዊ ግንኙነት አጠቃቀሞችን በደብተራችሁ ላይ ፃፉና መልሶቻችሁን ለመምህሩ አሳዩ።

4.4 የመልካም ማህበራዊ ግንኙነት መሰናክሎች

የቀደመ ዕውቀት መፈተሻ መልመጃዎች

1. ውድ ተማሪዎች፣ ከጓደኛችሁ ጋር ስትጫወቱ ችግር አጋጥሟቸሁ ያውቃል?

2. ለችግሩ ተጠያቂው ማን ነበር?

3. ችግሩን እንዴትስ ፈታችሁት?

በባለፈው ትምህርት ስለመልካም ማህበራዊ ግንኙነቶች ጥቅም ተምራችኋል። በዚህ ትምህርት ከሌሎች ጋር አዎንታዊ ማህበራዊ ግንኙነት እንዳንመሰርት የሚከለክሉን መሰናክሎች ወይም ችግሮች እንዳሉ መረዳት አለባችሁ።

ለመልካም ማህበራዊ መስተጋብር እንቅፋት የሆኑ አንዳንድ ባህሪዎች እና ተግባራት ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- አለመከባበር
- ታማኝነት የጎደለው ድርጊት
- ብልግና
- የራሱ ያልሆነ አሻንጉሊት መጫወቻዎችን በመያዝ መጣላት
- ሰልፍ ተሰልፎ ሌሎችን መግፋት
- ሌሎችን መበደል
- ትብብር አለመኖር ወይም አለመተባበር
- ብቸኝነት
- ዓይን አፋርነት
- ሕጎችን አለማክበር
- አካላዊ ጥቃት ማድረስ
- የሌሎች ንድሮች ፍላጎት የበላይ ሆኖ ለመጫን መሞከር
- ስግብግብነት ወይም ራስ ወዳድነት

እነዚህ ሁሉ ባህሪያት አዎንታዊ ወይም መልካም ማህበራዊ ግንኙነቶችን ያበላሻሉ። ለምሳሌ፣ ልግስና የሚጠቅም ቢሆንም፣

ስግብግብነት ሌሎች ሰዎችን ከማስቀየም አልፎ የራሱን ንብረት ጭምር ሊያሳጣ የሚያስችል ነው።



ስግብግቡ ውሻ ውሃ ውስጥ የራሱን ምስል ሲመለከት

በአንድ ወቅት በገጠር መንደር ይኖር የነበረ አንድ የተራበ ውሻ ትንሽዬ ጥንቸል አድኖ የቻለውን ያህል በልቶ ወደ ቤቱ ተመለሰ። ወደ ቤቱ ሲመለስ ጠባብ ድልድይ ያለበት ወንዝ ደረሰ። ወንዙን ሲሻገር ሌላ ውሻ በአፉ ውስጥ አጥንት ያለው ወንዙ ውስጥ አየ። በወንዙ ውስጥ ያየው ነገር የራሱ ነጸብራቅ ወይም ምስል መሆኑን አላወቀም። ከስግብግብነቱ የተነሳ አጥንቱን በወንዙ ውስጥ ካለው የውሻ ጥላ ለመንጠቅ ፈለገ። ነገር ግን ሲጮህና አጥንቱን ለመንጠቅ ወደ ወንዙ ሲዘል፣ ስግብግብቡ ውሻ በአፉ ይዞት

የነበረውን የራሱን አጥንት ወንዙ ውስጥ ጣለ ወንዙም አጥንቱን ወሰደው።

ተግባር 8፡ ከላይ ባለው ታሪክ ላይ በመመስረት ከታርኩ የተማራችሁትን በቡድን ተወያዩበት።

የምዕራፍ አራት ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ፣ መልካም ማህበራዊ ግንኙነትን የመመስረት ሰላማዊ እና ተግባቢ መንገድ መሆኑን ተምራችኋል። የረሻም ጊዜ እና የጋራ ተጠቃሚነትን ለመገንባት አስፈላጊ መሆኑና ከሌሎች ጋር በአግባቡ መገናኘት የሚያስችላችሁ አስፈላጊ ማህበራዊ ክህሎቶችን መገንባት እንዳለባችሁ ማየት ችላችኋል።

የምዕራፍ አራት ማጠቃለያ ጥያቄዎች

ሁሉንም መልሶች በማስታወሻ ደብተርዎ ላይ ፃፉ

ክፍል አንድ፡ አረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ 'እውነት' ትክክል ካልሆነ 'ሐሰት' ብላችሁ ጻፉ

1. **ከሁሉም ሰው ጋር የቅርብ ጓደኝነት በቀላሉ መመስረት ይቻላል።**
2. **ሃሊማ እና ሳራ የአንድ ጥሩ ጓደኛ ባህሪ ላይ አልተስማሙም።**
3. **ራስ ወዳድነት የማህበራዊ ግንኙነትን ይጎዳል።**

ክፍል ሁለት፡ ከዚህ በታች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጡና በደብተራችሁ ላይ ጻፉ።

1. **ከሚከተሉት ውስጥ የማህበራዊ መስተጋብርን ለማንፀባረቅ አስፈላጊ ያልሆነው የትኛው ነው?**
   - **ሀ. ታማኝነት የጎደለው ድርጊት**
   - **ለ. ልግስና**
   - **ሐ). የቡድን መንፈስ ወይም በቡድን መስራት**
   - **መ) መተባበር**

2. ከሚከተሉት ውስጥ ከክፍል ጓደኛህ ጋር ግጭት ውስጥ ስትገባ ማድረግ ያለብህ የትኛውን ነው፡-

   ሀ. እሱን/ሷን አለመቀበል

   ለ. መደባደብ እና ማሸነፍ

   ሐ) ችግሩን በሰላማዊ መንገድ መፍታት

   መ) ትምህርት ቤቱን መቀየር

3. ከሚከተሉት ውስጥ የረጅም ጊዜ እና የጋራ ጥቅም ያለው ጓደኝነትን የማይጎዳው የትኛው ነው?

   ሀ) አክብሮት

   ለ) መተማመን

   ሐ) ስጥቶ መቀበል

   መ) ከላይ ያሉት ሁሉም መልስ ናቸው

ክፍል ሶስት፡ <u>በምድብ ሀ ስር</u> የተሰጡትን የክፍል ታሪኮችን <u>ከምደብ ለ ስር</u> ከተዘረዘሩት ተዛማጅ የግብረ ገብ ትምህርቶች ጋር አዛምድ፡ አምድ ሀ አምድ ለ

1. ስግብግቡ ውሻ	ሀ) ጓደኝነት መስጠት እና መቀበል ያስፈልገዋል
2. ሦስቱ ወንዶች ልጆች	ለ) ባለህ ነገር ደስተኛ ሁን
	ሐ) አንድነት ጥንካሬ ነው።

ምዕራፍ አምስት

ለጋራ ጥቅም ትኩረት መስጠት

ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የጋራ ጥቅምን ትርጉም ታብራራላችሁ፡፡
- የጋራ ጥቅም ስላለው ጠቀሜታ ትወያያላችሀ፡፡
- በትምህርት ቤትም ሆነ በማህበረሰቡ ውስጥ ሌላውን የመደጋገፍ/የበጎንት ልምድን ታሳያላችሁ፡፡
- በጋራ ጥቅም እና በግለኝነት መካከል ያለውን ልዩነት ትገልጻላችሁ፡፡
- የጋራ ጥቅም ዐይነቶችን ትለያላችሁ፡፡
- የጋራ ጥቅሞችን የሚጎዱ ምክንያቶችን ትለያላችሁ፡፡

5.1 የጋራ ጥቅም ትርጉም

የቀደመ ዕውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

በእርስዎ መንደር ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በጋራ የሚጠቀሙባቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?

የጋራ ጥቅም የሚለው ሐረግ ለሰው ልጆች፣ ለግለሰቦች፣ ለቡድኖች፣ ለማኅበረሰቦች እና ለአገር እንዲሁም ለዓለም ሰዎች ጠቃሚ የሆኑትን ንብረቶችን (ቁሳቁስ፣ ባሕላዊ ወይም ተቋማትን ያመለክታል)። ይህ ማለት የጋራ ሀብቶች ሆኖ ጸታ፣ እድሜ, ሀይማኖት፣ ባህል እና የዘር ልዩነት ሳይኖር ለሁሉም ሰዎች ደህንነት ጥቅም ላይ የሚውል ማለት ነው:: የጋራ ጥቅሞች ለሕዝብ ደኅንነት፣ ለሕዝብ ንብረቶች፣ ሀብቶች፣ ለአገልግሎቶች፣ እና የሁላችንም የሆኑ እና የምንጋራው የማህበረሰብ እሴቶችን ያካትታሉ።



ሴቶች በጋራ የፓምፕ ውሃ ሲቀዱ።



ልጆች በሀብረት ሆነው ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱ



የሳር መሬት እና ትልቅ ወንዝ

ተግባር 1፡ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ጥንድ ሆናችሁ ተወያዩ

ሀ) በመንደራችሁ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ከላይ ካለው ሥዕላዊ መግለጫ ምን ይጠቀማሉ?

ለ) በመንደራችሁ ውስጥ እነዚህ አገልግሎቶች ከሌሉ ምን እንደሚፈጠር አብራሩ?

የጋራ ሀብቶች የምንላቸው ትምህርት ቤቶች፣ ሆስፒታሎች፣ የፖሊስ ጣቢያዎች እና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ። እንደ መብራ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ ምግብ እና ውሃ፣ ንጹህ አካባቢ፣ ትራንስፖርት እና ኮሙኒኬሽን የመሳሰሉ ማህበራዊ አገልግሎቶችን ያካትታሉ። የጋራ እሴቶች የምንላቸው ደግሞ እንደ መተሳሰብ፣ መከባበር፣ መተባበር፣ መረዳዳት፣ ልዩነቶችን መቻቻል ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉት ማህበራዊ እሴቶቻችንን ያካተተ ነው።

ተግባር 2፡ ከላይ ባለው ጽሑፍ ላይ በመመስረት የእናንተን ተጨማሪ የጋራ ሀብቶች ምሳሌዎችን በመስጠት ስለ አገልግሎታቸው በቡድን ሆናችሁ ተወያዩ።

5.2 ለጋራ ጥቅም የማሰብ አስፈላጊነት

የቀደመ ዕውቀት ወይም ማነቃቂያ ጥያቄዎች

1. ውድ ተማሪዎች ህመም ተሰምቷችሁ ያውቃል?
2. ለህክምና የት ሄዳችሁ?

የጋራ ሃብት ከግለሰብ እስከ ማህበረሰብ ድረስ ለሁሉም የሰው ልጅ በርካታ ጠቀሜታዎች አሏቸው። በመጀመሪያ በተናጠል/በብቸኝነት ጥሩ ህይወት መኖር አይቻልም። ስለዚህ የጋራ ሀብቶችን በጋራ በመጠቀም የሚፈጥረውን የደስታ ስሜት እና የሚያመጣውን ጥንካሬ መገመት አያዳግትም።



አንድ ትልቅ ወንዝን በድልድይ ላይ የሚያቋርጡ ሰዎች

ሁለተኛው የጋራ ሀብቶች የሰውን ልጅ ደህንነት ለመጠበቅ ይረዳሉ:: ለምሳሌ የጋራ ተቋማት እንደ ፖሊስ ጣቢያ እና ፍርድ ቤቶች በሌሉበት ለሕይወታችን እና ለንብረታችን ሰላምና ደህንነት ላይኖር ይችላል።



የሴት ልጅን ቦርሳ የዘረፈ ሌባ በፖሊስ ሲያዝ

ሦስተኛው የጋራ ሀብቶችን መጠበቅና ማሳደግ ነው። ለሰው ልጅ እድገት ጉልህ አስተዋፅዖ ይኖረዋል። ልማት ደግሞ ህይወታችንን ምቹ ያደርገዋል።

5.3 ለሌሎች ደህንነት መኖር/Altruism/በጎነት

ለሌሎች ደህንነት መኖር ማለት፡- ከራስ ደህንነት በላይ የሌሎች ደህንነት በዋናነት አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያምን ነው። ለሌሎች የሚኖሩ ሰዎች ይህን ለማድረግ ግዴታ ስላለባቸው ሳይሆን ለሌሎች መልካም ነገር ለማድረግ ስላሰቡ ነው። ከራሳቸው ጥቅም ይልቅ የሌሎችን ጥቅም ያስቀድማሉ ማለት ነው። በአዲስ አበባ ከተማ ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናትን እና ቤት የሌላቸውን ሰዎች የአረጋውያንን ማቆያ ማዕከል በማቋቋም የሚያኖሩ ግለሰቦችም አሉ። ለአብነት ምሳሌ የሚሆኑ ሰዎች ሚቺ የክብር ዶክተር አበበች ጎበና እና የክብር ዶክተር ቢኒያም በቀለ ናቸው።



የክብር ዶክተር አበበች ጎበና



የክብር ዶክተር ቢኒያም በቀለ

ተግባር 3፡ ወላጆቻችሁን እና ጎረቤቶቻችሁን በመጠየቅ፣ በመንደራችሁ ውስጥ የሚገኙትን የበጎ ስራዎችን የሚሰሩ ሰዎች ተጨማሪ ምሳሌዎችን እና በሌሎች ሰዎች ላይ ምን እያደረጉ እንደሆነ ግለጹ።

አንዳንድ በጎ ሰዎች ለሌሎች ሲሉ ሕይወታቸውን ለአደጋ እስከ ማጋለጥ ድረስ ይሄዳሉ። የሚከተለው ታሪክ እንደነዚህ ያሉትን ሰዎች ምሳሌ ያሳያል::

የጓደኛን ቦታ መተካት

በአንድ ወቅት በትንሽ መንደር ውስጥ ይኖር የነበረ አንድ ጨካኝ ንጉስ ነበረ የመንደሩን ሰዎች ሁሉ ያማረረ ከዕለታት አንድ ቀን አንድ የመንደሩ ሰው ንጉሱ ላይ ተቃውሞውን አሰማ። ንጉሱም በጣም ተናድዶ ለወታደሮቹ ተቃዋሚውን አስረው እንዲሰቅሉት ትዕዛዝ ሰጣቸው። ሰውዬው ክሱን ተቀብሎ ንጉሱን ለመጨረሻ ጊዜ ሚስቱን እና አምስት ልጆቹን እንዲያይ ለመነው። ንጉሱ ለመመለሱ ምንም ዋስትና የለም በማለት ይህንን ጥያቄ ውድቅ አደረገው። በዚህ ጊዜ ከሕዝቡ መካከል አንድ ሰው ቀርቦ ንጉሡን "ጌታዬ ሆይ! እባካችሁ በዋስትና በሱ ፈንታ እኔን ያዙኝ ካልተመለሰም ልትሰቅሉኝ ትችላላችሁ አላቸው። ንጉሱም በመደነቅ እንደዚህ አይነት የራሱን ህይወት ለሌላ ሰው አሳልፎ የሚሰጥ ሰው መኖሩን በማየቱ ሰውዬው ወደ ቤቱ እንዲሄድ እና ከሶስት ሰአት በኋላ ተመልሶ እንዲመጣ ፈቀደለት ። ሰውዬው ቤተሰቡን አይቶ ወደ ንጉሱ ተመለሰ። ነገር ግን በጉዞ ላይ እያለ ከፈረሱ ላይ ወድቆ ከባድ ጉዳት ደረሰበት። ይህ አደጋ በመድረሱ ሰውዬውን ለአንድ ሰዓት ያህል አዘገየው፣ እናም ሰውዬው የሚሰቀልበት ቦታ ሲደርስ

ዋስ የሆነው ሰው ሊሰቀል ተዘጋጅቶ ነበር። የተጎዳው ሰው መመለሱን በመንገር ንፁህ ሰው እንዲፈታ ንጉሱን እያለቀሰ ለመነው። ንጉሱም ተስማምተው ስለነበር ሰውዬው ነጠላ ሰው በመሆኑ አምስት ልጆች ያሉት እና በፍቅራቸው የተጎዳውን ጓደኛውን እንዲተካ ንጉሱን ለመነው። ንጉሱ እንዲህ ባለው ከራስ ወዳድነት ነፃ በሆነው ጓደኝነት ተማርኮ ሁለቱን ሰዎች ፈታቸው።

ተግባር 4፡ ከላይ ካለው ታሪክ በመነሳት የተማራችሁትን የግብረ ገብ ትምህርት ተወያዩና ምላሻችሁን ለክፍሉ አጋሩ።

5.4 ግለሰባዊነት እና የጋራ ጥቅም

ግለሰባዊነት የሚለው ቃል የሚያመለክተው ለራስ ጥቅም እና ደህንነት ቅድሚያ የመስጠት እምነት ነው። ስለሌሎች ሰዎች ደህንነትም ሆነ ጥቅም ምንም ደንታ የሌለው እራስን ያማከለ አመለካከት ማለት ነው። እውነቱን ለመናገር እኛ ራሳችንን ስንመለከት ተፈጥሯዊ ፍላጎት አለን። ስለ ህይወታችን ፣ ጤናችን ፣ የህይወት ፍላጎቶች እና ወላጆቻችን ማሰብ አለብን ። ስለ ግለሰባዊ መብቶቻችን የመማር፣ ራስን የመጠበቅ፣ ደህንነት እና ሰላምን ማሰብ አለብን።

ይሁን እንጂ ከጋራ ጥቅም ጋር ሲወዳደር ግለሰባዊነት የሚለው ቃል አሉታዊ ይዘት አለው። ይህ የሚያመለክተው ከጋራ ጥቅም

አመለካከት ጋር የሚቃረን የራስ ወዳድነት አመለካከት ነው። ይህ መተማመንን፣ ትብብርን እና ታማኝነትን ሊጎዳ ይችላል። እንደዚህ አይነት ባህሪ እራሱን/ግለኝነትንም ሊነካ ይችላል። “ብቻውን የሚበላ ብቻውን ይሞታል” የሚለው አባባል ይህንን እውነታ ያስረዳል። ስለዚህ እንደ መልካም ሰው ራስ ወዳድነትን፣ ስግብግብነትን እና የሌሎችን ፍላጎት ችላ ማለትን ማስወገድ አለባችሁ። በምትኩ የመረዳዳት፣ የመጋራት፣ የመተሳሰብ እና የመተባበር ልምድን ማዳበር ይኖርባችኋል።

5.5 የጋራ ጥቅም መገለጫ

በዚህ ክፍል ንዑስ ክፍል ውስጥ ስለ ሶስት የጋራ ጥቅም መገለጫዎችን ትማራላችሁ። እነዚህ የህዝብ ደህንነት፣ የህዝብ ሀብትን በጥበብ መጠቀም እና አካባቢን መጠበቅ ናቸው።

5.5.1 የህዝብ ደህንነት

የህዝብ ደህንነት ማለት የአንድ ማህበረሰብ ሰላማዊ፣ የተረጋጋ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ህይወት ማለት ነው። ይህ ማለት የሁሉንም ሰዎች ደህንነት መጠበቅ ነው። በሌላ አነጋገር ሰዎችን ከወንጀሎች፣ ከአደጋዎች እና ሌሎች ከባድ ጥቃቶች እና በህይወታቸው ላይ ከሚደርሱ አደጋዎች መጠበቅ ማለት ነው።

ለምሳሌ እንደ ተማሪ ለስኬታማ ትምህርት ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት ቤት አካባቢ ሊኖር ይገባል። የትምህርት ቤት ደህንነት ከአደጋ ነጻ የሆኑ የመማሪያ ክፍሎችን፣ የመጫወቻ ሜዳዎችን፣ ንፁህ ውሃ እና መጸዳጃ ቤቶችን ያጠቃልላል። ትምህርት ቤቶች ለተማሪዎች ከአካላዊ ንክኪ እና ረብሻዎች የሚከላከሉ እና የመከላከያ ህጎችና መመሪያዎች ሊኖራቸው ይገባል። እነዚህ ህጎችና መመሪያዎች በሌሉበት አካባቢዎች የእናንተን ሰላም፡ ጤና፣ ደህንነት እና ህይወታችሁን ሊጎዳ ይችላል። በዚህ ምክንያት የራስህን፣ የሌሎችን እና የህዝብን ደህንነት ለመጠበቅ የሚረዱ ህጎችን የማክበር ግዴታ አለባችሁ።

5.5.2 የህዝብ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም

የህዝብ ሃብት በተፈጥሮ እና በሰው ሰራሽ ቁሳቁስ ፣ አገልግሎቶች እና ሌሎች በርካታ ነገሮች ለሰው ልጅ ደህንነት አስተዋፅዖ ያደርጋሉ። የሕዝብ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም ማለት በጥንቃቄ፣ ኃላፊነት የተሞላበት እና ሥነ ምግባራዊ አጠቃቀም እና አያያዝ ማለት ነው። እናም እነዚህን ሀብቶች በሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች መጠበቅ ማለት ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት ሀብቶችን በአግባቡ መጠቀም እንዳይበላሽ እና እንዳይጎዳ ለመደገፍ ይረዳል። የሀብት ተጠቃሚ እንደመሆናችሁ መጠን ሀብቶችን መጠበቅ እና በአግባቡ መጠቀም አለባችሁ።

የሚከተለው ታሪክ ጥሩ ትምህርት ይሰጥዎታል።



የንብ ቀፎ፣ወፎች እና ሶስት ሰዎች በአንድ ትልቅ ዛፍ ጥላ ስር ተጠልለው።

አመሰጋኝ ሁኑ

ወቅቱ በጋ እንደመሆኑ ፀሐይዋ በጣም ታቃጥል ነበር። ሁለት መንገደኞች ዛፎች በሌሉት አቧራማ መንገድ ላይ ይጓዙ ነበር። ይሁንና ከጠራራ ፀሐይ ለመጠለል መጠጊያ ሲፈልጉ ትልልቅ ቅጠሎችና ቅርንጫፎች ያሉት ዛፍ እንደ ጣንጥላ ተዘርግቶ

ተመለከቱ። ወዲያውኑ እቃቸውን መሬት ላይ አስቀምጠው በቀዝቃዛው ወፍራም የዛፉ ጥላ ስር ተቀመጡ። ትንሽ እረፍት ካደረጉ በኋላ አንዱ መንገደኛ ሌላኛውን "እንዴት የማይጠቅም ዛፍ ነው! ምንም ፍሬ አያፈራም" አለው። ዛፉም ይህንን ሰማቸው ሀዘን ተሰምቶትም ጮኸ "አንቺ ምስጋና የሌለሽ ነፍስ! በአንድ በኩል በቀዝቃዛው ጥላዬ ውስጥ ከሚቃጠለው የፀሐይ ሙቀት ተጠልለሽ ነገር ግን በከንቱ እየጠራሽኝ ነው። ወዲያውኑ ተነሺና ከዚህ ቦታ ውጪ አለች። !" ይህ በእንዲህ እንዳለ ከመንገደኞቹ አንዱ በዛፉ ቅርንጫፍ ላይ የንብ ቀፎን አይቶ ለጓደኞቹ ዛፉ ተጨማሪ አገልግሎት እየሰጣቸው መሆኑን አሳየው። በመጨረሻም ሁለቱም ተጓጉች በስህተታቸው አዘነው ዛፉን ይቅርታ ጠየቁ።

ተግባር 5፡ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ሆናችሁ ተወያዩ

ሀ) ከላይ ካለው ታሪክ ምን ትምህርት ተማራችሁ?

ለ) እንደ እናንተ አስተያየት ከላይ ባለው ታሪክ ውስጥ ያልተጠቀሱ ሌሎች የዛፉ ተግባራት ምንድን ናቸው?

5.5.3 አካባቢን መጠበቅ

አካባቢን መጠበቅ ማለት ጤናማ፣ ዘላቂ እና የጋራ መጠቀሚያ የሆነውን የሰውን ልጅ ደህንነት ከሚጎዱ አደጋዎች መጠበቅ ማለት ነው። የአካባቢ ጥበቃ ላይ ያለውን እንክብካቤ እና ከጉዳት መጠገንን

ይመለከታል። የአካባቢ ጥበቃን የሚያሳዩ ሁለት መግለጫዎች ከዚህ በታች ባሉት ሥዕሎች ላይ ተገልፀዋል።





ተማሪዎች የዛፍ ችግኞችን በጋራ ሲተክሉ



የመሬት መሸርሸርን ለመከላከል እረከን የሚሰሩ ሰዎች

ተግባር 6፡ ከላይ በሥዕላዊ መግለጫው ላይ ያለው እያንዳንዱ ድርጊት አካባቢን ለመጠበቅ እንዴት እንደሚረዳ ተወያዩበት።

5.6 የጋራ ጥቅም እንቅፋቶች ወይም ችግሮች

በትክክለኛ አሠራር እና የጋራ ሀብቶች ዘላቂ አጠቃቀም ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ የተለያዩ መሰናክሎች አሉ:: ለጋራ ጥቅም በጣም አሳሳቢውና እንቅፋት ከሆኑት መካከል ግለሰብአዊ አመለካከት፣ ራስ ወዳድነት፣ ስግብግብነት እና ግድየለሽነት መኖር በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው። ለጋራ ሀብቶች ተጨማሪ እንቅፋቶች ከመብራት ገመዶች መሰረቅ ጋር የተያያዙ የወንጀል ድርጊቶች የጋራ ሀብቶችን የሚጎዱ ናቸው። እነዚህ ሁሉ ለጋራ ሀብት

አገልግሎቶች እና ለህይወት እና ለንብረት ደህንነት ስጋት የሆኑ የወንጀል ድርጊቶች ናቸው። ስለዚህ እንደዚህ ባሉ የወንጀል ድርጊቶች ውስጥ ከመሳተፍ የመቆጠብ ግዴታ አለባችሁ። እንዲሁም ሌሎች እንደዚህ አይነት ድርጊቶች ሲፈጽሙ ስታዩ ድርጊቱን ቢያንስ ለወላጆቻችሁ እና ለትምህርት ቤቱ ማሳወቅ አለባችሁ።

የምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የጋራ ጥቅም የሚለው ቃል ለሰው ልጆች፣ ለግለሰቦች፣ ለቡድን ፣ ለማህበረሰብ እና ለአንድ ሀገር እንዲሁም ለአለም ህዝብ ጠቃሚ የሆኑትን ነገሮች እንደሚያመላክት ተምራችኋል። ይህ ማለት የፆታ፣ የእድሜ፣ የሀይማኖት፣ የባህል እና የዘር ልዩነት ሳይኖር ሁሉም ሰዎች የሚጋሩት እና የሚጠቀሙበት ማለት ነው። በመሆኑም ሁላችንም የጋራ ንብረቶቻችንን መጠበቅ አለብን። ይህ ማለት ለጋራ ሀብቶቻችን መቆርቆር እና ደህንነታቸውን ማስጠበቅ አለብን። አካባቢን በመጠበቅ የተፈጥሮ ሃብቶችን በአግባቡ በመጠቀም ወዘተ።

ምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ ጥያቄዎች

ክፍል አንድ፡ አረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ 'እውነት' ወይም ትክክል ካልሆነ 'ሐሰት' ብላችሁ በደብተራችሁ ላይ ጻፉ።

1) የጋራ መጠቀሚያዎችን መስረቅ ስህተት አይደለም።

2) የጋራ መጠቀሚያ መሰናክሎች የሚከሰቱት በሰው ልጅ ሆን ተብሎ በሚፈፀም ድርጊቶች ነው።

3) ዛፎችን መትከል ለጋራ መጠቀሚያዎች ደህንነት አስፈላጊ ነው።

4) የጋራ ጥቅምን የሚያስጠብቁ ድርጅቶችን ማቋቋም የመንግስትና የህብረተሰቡ ኃላፊነት ነው።

5) ለድሆች የበጎነት አገልግሎት መስጠት የሚችሉት ሀብታሞች ብቻ ናቸው።

ክፍል ሁለት፡ ባዶ ቦታው ላይ ትክክለኛውን መልስ ሙሉ።

1. የጋራ ጥቅምን፣ ህይወታችንን እና ንብረታችንን ከወንጀለኞች የሚጠብቅ ተቋም _____ ነው።
2. አፈርን ከአፈር መሸርሸር የመከላከል ተግባር_____ ነው።

3. ጥበብ የጎደለው የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ምሳሌ ሊሆን ይችላል። _____

4. ከሌሎች ይልቅ ለራስ ደህንነት ቅድሚያ መስጠት _____ በመባል ይታወቃል።

ምዕራፍ ስድስት

ባህላዊ ቅርሶች

ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

የባህል ቅርሶች ማለት ምን እንደሆነ ታብራራላችሁ፡፡

- የተለያዩ የባህል ቅርሶችን ትለያላችሁ፡፡
- የባህል ቅርሶችን መጠበቅ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ዋጋ ትሰጣላችሁ፡፡
- የባህል ቅርሶች ጥበቃ መንገዶችን ታሳያላችሁ፡፡

6.1 የባህልና ቅርሶች ትርጉም

በዚህ ንዑስ ክፍል ባህል እና ቅርስ የሆኑትን የሁለት ጠቃሚ ጽንሰ-ሀሳቦች ትርጉሞች ትማራላችሁ፡፡

ባህል

ባህል የሚለው ቃል እውቀትን፣ እምነትን፣ ስነ ጥበብን፣ ሞራልን፣ ህግን እና ልማድን የሚያካትቱ ብዙ ሃሳቦችን ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም ማንኛውንም ሌላ አቅሞችን እንዲሁም የሰው ልጅ

እንደ ማህበረሰብ አባልነት ያገኘውን ሌሎች ችሎታዎች እና ልማዶችንም ያካትታል።

ባህል ግን የግለሰብ ንብረት አይደለም ይልቁንም አብረው የሚኖሩ የአንድ የተወሰነ የሰዎች ቡድን የአኗኗር ዘይቤ እና የጋራ ባህሪ ነው። ባህል በተለያዩ ቁሳዊ እና መንፈሳዊ የሰው ምርቶች መልክ ይገለጣል:: እነዚህ ሁሉ የሰውን እውቀት፣ እምነት፣ እሴቶች፣ ደንቦች፣ ባህሪ እና ክህሎቶች ያሳያሉ። እርግጥ ነው ሁሉም የሰዎች ቡድኖች የተለያዩ የአኗኗር ዘይቤዎች፣ ቴክኖሎጂዎች እና እምነቶች አሏቸው፣ እነሱም የመተዳደሪያ መንገዶችን ልዩነት ያመለክታሉ። በሚቀጥለው ንዑስ ክፍሎች ውስጥ እነዚህን ትማራላችሁ ።

ተግባር 1፡ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ

ሀ) በመንደራችሁ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በሃይማኖታዊ የበዓላት ቀናት ላይ ምን ያደርጋሉ?

ለ) በእነዚህ ሃይማኖታዊ የበዓላት ቀናት ምን ይበላሉ፣ ይጠጣሉ፣ ይለብሳሉ?

ሐ) በእነዚህ ሃይማኖታዊ የበዓላት ቀናት እንዴት ራሳቸውን ያዝናናሉ?

ከዚህ በታች ባለው ስዕላዊ መግለጫ ላይ እንደሚታየው መሬትን በበሬ በማረስ ባሕላችን ተገልጿል።



መሬትን በበሬ ማረስ



መሬት በትራክተር ማረስ

ተግባር፡2

ከላይ ያሉት ሥዕሎች ምን ያሳያሉ? መልሶቹ ላይ ጥንድ ሆናችሁ ተወያዩ

ሀ) ምን ባህል ያሳያሉ?

ለ) በመካከላቸው ተመሳሳይነት እና ልዩነቶች አሉ?

ቅርስ

ቅርስ የዚህ ንዑስ ክፍል ሁለተኛው ዋና ጽንሰ-ሐሳብ ነው። ቅርስ እንደ ጥምር ፍጥረት እና የሰው ልጅ ምርቶች ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ የሚተላለፍ ነው። ስለዚህ የባህል ቅርስ የሰው ልጅ ያለፈውን ከአሁኑ እና ከመጪው ጋር ያገናኛል። በዚህም ምክንያት የባህል ቅርሶች ከቀደመው ትውልድ ጀምሮ ዛሬ ላይ የደረሱ እሴቶችን፣ እምነትን፣ እውቀትን፣ ክህሎትን እና ትውፊትን የሚለዋወጡ ህዝቦችን ያንፀባርቃል። በጥንት ጊዜ የሰው ልጅ እህልን የማከማቸት ልምድ በጎተራ ነው።

6.2 የባህል ቅርስ ዓይነቶች

እንደ መልካቸው ወይም ቅርጻቸው እና ከተሠሩበት ዓላማ በመነሳት የባህል ቅርሶች በሁለት አጠቃላይ ምድቦች ማለትም በቁሳዊ እና ቁሳዊ ያልሆኑ ባህላዊ ቅርሶች ይከፈላሉ ።

የቁሳዊ ባህላዊ ቅርሶች በአካላዊ መልክ የሚታዩ ቁሳዊ ቅሪቶች ናቸው። በአይናችን እናያቸዋለን እንዲሁም በእጃችንም እንነካቸዋለን እነሱ የሰው ልጅ የፈጠራ ውጤቶች የመጀመሪያ ምርቶች ናቸው። አንዳንድ የኢትዮጵያ የቁሳዊ ባሕላዊ ቅርሶች በብሔራዊ ሎቶሪ ትኬቶች፣ ቴምብሮች እና የብር ኖቶች ይተዋወቃሉ። ለምሳሌ ከዚህ በታች ያለው ሥዕላዊ መግለጫ በ2012 ዓ.ም የወጣውን አዲሱን የኢትዮጵያ 100 ብር ኖት ያሳያል።

በውስጡ የአክሱም ሐውልት እና የጎንደር ቤተ-መንግስት (በተለምዶ ፋሲል ግንብ) በመባል የሚታወቁትን ሶስት ኢትዮጵያውያን የሚዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች ፎቶግራፍ ከፊት ለፊት እና በሃረር ከተማ ዙሪያ ያለው ታሪካዊ ግድግዳ (በተለምዶ የጀጎል ግንብ በመባል ይታወቃል) በጀርባው በኩል ይሣል።



የኢትዮጵያ100-ብር የፊት ገጽ



የኢትዮጵያ 100-ብር የኋላ ገጽ

ተግባር 3፡ **ከላይ ባሉት ሥዕሎች ላይ በመመስረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ተወያዩ፡፡**

ሀ) ሦስቱ የባህል ቅርሶች ምን ያሳያሉ?

ለ)እነዚህ ባህላዊ ቅርሶች የተሠሩት ለምንድነው ብላችሁ ታስባላችሁ?

የኢትዮጵያ ቁሳቁስ ባሕላዊ ቅርስ ምሳሌዎች የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ይገኙበታል፡፡



የላሊበላ ቤተ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን

ጥንታዊ ሀረር ጀጎል



ሀረር ጀጎል፣ የተመሸገ ታሪካዊ ከተማ

ጥያ ትክል ዲንጋይ፣ የአርበኞችን ስራ የሚገልጹ ምልክቶች የተቀረጹ ተከታታይ የቆሙ ድንጋዮች::



ጥያ ትክል ድንጋይ

የኮንሶ ባህላዊ መልክዓ ምድር ከባህላዊ መንደር ጋር በሰፋፊ ደረቅ ድንጋይ እርከኖች የተገነቡ ናቸው።



የኮንሶ ባህላዊ መልክዓ ምድር

በሌላ በኩል ቁሳዊ ያልሆኑ ባህላዊ ቅርሶች በአይን የማይታዩትን እና በእጅ የማይዳሰሱ የሰው ልጅ ያለፈ ትዝታዎችን ያመላክታሉ። እነሱም ቋንቋ፣ ትውፊት፣ የሞራል ታሪኮች፣ ልማዶች፣ ሙዚቃ፣ ዳንስ፣ ግጥም፣ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች እና የሀገር በቀል ዕውቀት ሲሆኑ እነሱ የአኗኗር ዘይቤ ፣ እምነት ፣ ሥርዓቶች ፣ የእሴት ሥርዓቶች እና የማህበራዊ ደረጃዎች መግለጫዎች ናቸው። ከቅድመ አያቶቻችን የወረስናቸው አንዳንድ የማህበራዊ እሴቶችና ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ::

- ታላላቆቻችንን ማክበር

- እንግዳ ተቀባይነት
- ጀግንነት
- ለጋስነት፣
- አቅመ ደካሞችን መርዳት
- ለሀይማኖት እና ለብሄር ብሄረሰቦች መቻቻል የሃይማኖታዊ ባህላዊ ቅርሶች ምሳሌዎች ያጠቃልላሉ። የሙስሊም ኢድ አል-አድሃ ጸሎት እና የጥምቀት በዓል።





የኢትዮጵያ ኢድ አል አድሃ የጸሎት ስነስርዓት እና የጥምቀት በዓል አከባበር

ተግባር 4፡ በመንደራችሁ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በእነዚህ ሃይማኖታዊ በዓላት ጊዜ ምን እንደሚያደርጉ አብራሩ።

የባህላዊ በዓላት ምሳሌዎች አሸንዳ የአማራ እና የትግራይ ልጃገረዶች በዓል፣ ፍቼ ጨምባላ የሲዳማ አዲስ አመት በዓል እና የኢድ አል አራፋ በዓል ይገኙበታል።



የሲዳማ አዲስ አመት ፍቼ ጨምባላ በዓል አከባበር



የአሸንዳ እና ሻደይ በዓል አከባበር

6.3 የባህላዊ ቅርሶች መጠበቂያ መንገዶች

ባህላዊ ቅርሶችን መጠበቅ ማለት ቅርሱ በመጀመሪያ የነበረውን መጠን፣ ቅርፅ፣ ቀለም፣ ጥራት እና ትርጉም ሳይለቅ በአግባቡ መያዝና ከአደጋ መከላከል ማለት ነው። የባህላዊ ቅርሶችን መጠበቅና ከአደጋ መከላከል በዋነኛነት የሚያተኩረው ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ከትውልድ ወደ ትውልድ በሚተላለፍበት ሂደት ላይ ነው።

ተግባር 5፡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያዩ እና መልሶቻችሁን በደብተራችሁ ላይ ፃፉ

1. የባህል ቅርሶችን የምንጠብቀው ለምንድን ነው?

2. የባህላዊ ቅርሶች መበላሸት፣ መበተን ወይም አጠቃላይ መጥፋት ሊያስከትሉ የሚችሉ ምክንያቶችን ዘርዝሩ?

የባህላዊ ቅርሶችን ደህንነትን የሚጎዱ እና ጉዳታቸውን ወይም አጠቃላይ ኪሳራን የሚያስከትሉ በርካታ ችግሮች አሉ። እነዚህም የሚያጠቃልሉት ሰው ሰራሽ ፈተናዎች ለምሳሌ የውጪ ጦርነት፤ ሀይማኖታዊ፣ የብሄር እና ፖለቲካ ግጭቶች፣ የባህላዊ ቅርሶች ሕገ-ወጥ ዝውውር፣ በእውቀት፣ በክህሎት እና በገንዘብ ማነስ ምክንያት ለባህላዊ ቅርሶች በቂ ያልሆነ ጥበቃ በባህላዊ ቅርሶች ላይ

አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል። በሌላ በኩል እንደ ጎርፍ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ እና ከባድ ዝናብ ቅርሶችን የሚያበላሹ ወይም የሚያወድሙ የተፈጥሮ አደጋዎች ናቸው።

በውጤቱም የባህላዊ ቅርሶች ጥንቃቄ የተሞላበት ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል:: ባህላዊ ቅርሶችን ለመጠበቅ የተለያዩ መንገዶች አሉ። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው።

- ለሰዎች ስለ ትርጉማቸው፣ ዓይነታቸው፣ ጥቅሞቻቸው እና በደህንነታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚያሳድሩ እና እነሱን ስለሚከላከሉባቸው መንገዶች ግንዛቤ መፍጠር ።
- አጠቃላይ የባህል ቅርስ ዶክመንቶችን መስራት እያንዳንዱ ባህላዊ ቅርስ ምን እንደያዘ፣ የተፈጠረበት ቀን፣ ዓላማው፣ ጥቅም ላይ የዋለው ቁሳቁስ፣ የሰሩት ሰዎች ወዘተ ያሉትን በዝርዝር ይገልፃል።
- የህዝብ ትብብርን ማሳደግ እና የባህላዊ ቅርሶችን ከስርቆትና

  ከውድመት መጠበቅ።
- ደህንነታቸው የተጠበቁ ሙዚየሞችን መገንባት
- የባህላዊ ቅርሶችን ለመጠበቅ የህግ ድንጋጌዎችን በጥብቅ ማስፈጸም እና

- የተበላሹ የቁስ ባህላዊ ቅርሶችን መጠገን

6.4 የባህል ቅርሶች አስፈላጊነት

የቀደመ ዕውቀት መፈተሻ መልመጃዎች፡፡

የባህላዊ ቅርስ ጠቀሜታዎች ምንድን ናቸው?

ባህሎችና ቅርሶች ኢትዮጵያዊነታችንን በመገንባት እና በአለም አቀፍ ደረጃ ያለንን ደረጃ በማሳየት ረገድ ትልቅ ሚና የሚጫወቱ ሲሆን ታሪካችንን፣ ስልጣኔያችንን እና የሰው ልጅ መገኛ ስለመሆናችን ተጨባጭ ማስረጃዎች ናቸው፡፡ ያለፈ ህይወታችን ማወቃችን ማንነታችንን፣ የጋራ ጥቅማችንን፣ አንድነታችንን ልዩነታችንን እና የስኬትና የውድቀት ታሪኮቻችንን ጭምር ያሳያል፡፡ ይህን ስናደርግ የባህላዊ ቅርስ የአንድነት እና የአብሮነት መገለጫችን ሆኖ ያገለግላል፡፡ በተጨማሪም አንድነት በየሀገሩ ለፖለቲካ መረጋጋት እና ለዘላቂ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት በጣም አሰፈላጊ ነው፡፡



የአድዋ ጦርነትና የኢትዮጵያ አንድነት

የአድዋ ድል የኢትዮጵያን አንድነት ያሳየ ጠቃሚ ታሪካዊ ክስተት ነው። በተጨማሪም ባህላዊ መታወቂያችን እና አንድነታችን ለማጎልበት፣ የአካባቢውን ሰዎች ስኬቶች ማስረጃ ለማቅረብ፣ የባህላዊ ቅርሶች ለባህላዊ ውይይት፣ እውቀት እና ክህሎትን ለመጋራት ሰፊ እድሎችን ይፈጥራሉ። እነዚህ የባህላዊ ቅርጻ ቅርጾች አስተዋጾ ለተለያዩ ባህሎች መከባበርን ያበረታታሉ። የባህል ቅርሶች ለአንድ ሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገት ትልቅ አስተዋፅዖ አላቸው። ለምሳሌ ከቱሪዝም ከፍተኛ ገቢ ለማግኘት ያገለግላሉ። በተጨማሪም በመንገድና ትራንስፖርት እንዲሁም በሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች ላይ የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንትን

ለማሳደግ፣ ለተለያዩ ግለሰቦች የሥራ ዕድል ለመፍጠር እና የአካባቢያቸውን የእጅ ስራዎችን አልባሳት እና ሌሎች ሸቀጦችን ለቱሪስቶች እንዲሸጡ ለአካባቢው ሰዎች የንግድ እድሎችን ይፈጥራሉ።



ቱሪስቶች የኢትዮጵያን ሙዚየም ሰንበኝ

ቱሪስቶች ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ ባህል እና የባህል ቅርሶቻችንን በአግባቡ በማስተዋወቅ የሀገራችንን መልካም ገፅታ ለመገንባት ያገለግላል። ይህ ደግሞ ሌሎች ቱሪስቶችና የውጭ ባለሀብቶች ወደ አገራችን እንዲመጡ ያበረታታል።

የምዕራፍ ስድስት ማጠቃለያ

የባህላዊ ቅርሶች እውቀትን፣ እምነትን፣ ልማዶችን፣ ትውፊቶችን፣ የአኗኗር ዘይቤዎችን፣ እሴቶችን ወዘተ ያካትታል። ባህላዊ ቅርሶች የሰውን ልጅ ያለፈውን ከአሁኑ እና የወደፊት ጊዜ ቅሪቶችን ያመለክታሉ። ይህን ሲያደርጉ የባህል ቅርስ በጥንት ጊዜ የሰው ልጅ ልምድ ማከማቻ ሆኖ ያገለግላል። በመልካቸው ወይም ከተሠሩበት ዓላማ አንጻር የባህላዊ ቅርሶች ናቸው። በአጠቃላይ በሁለት ይከፈላል ማለትም ቁሳዊ ባህላዊ ቅርሶች እና ቁሳዊ ያልሆኑ ባህላዊ ቅርሶች። የባህል ቅርሶች ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ጥቅሞች አሏቸው። ሆኖም እነርሱን ለሚጎዱ ወይም ለሚያጠፉ ለተለያዩ ሰዋዊ እና ተፈጥሯዊ ስጋቶች ተመጣጣኝ ወይም ሙሉ በሙሉ ለአደጋ ሊጋለጡ ስለሚችሉ በጥንቃቄ ልንጠብቃቸው ይገባል።

የምዕራፍ ስድስት ማጠቃለያ ጥያቄዎች

ክፍል አንድ፡ በአምድ 'ሀ' የሚገኙ ሃሳቦችን በአምድ 'ለ' ስር ከሚገኙ ተዛማጅ ሀሰቦች ጋር በማዛመድ መልሶቻችሁን በደብተራችሁ ላይ ፃፉ።

ምድብ ሀ	ምድብ ለ
1. የሰዎች የአኗኗር ዘይቤ	ሀ) የጦር መሳሪያዎች
2.ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ያስገኛል	ለ) ሃይማኖታዊ በዓላት
3.የቁሳቁስ ባህላዊ ቅርስ	ሐ) ቱሪዝም
4.ቁስ ያልሆኑ ባህላዊ ቅርሶች	መ) ባህል
5. ታላላቆችን ማክበር	ሠ) የኢትዮጵያ ባህላዊ እሴት

ክፍል ሁለት፡ አረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ 'እውነት' ትክልል ካልሆነ 'ሐሰት' ብላችሁ ጻፉ

1. **የሌሎችን ባህል ማክበር ለሰላማዊ-አብሮ መኖር አስተዋፅኦ ያደርጋል።**
2. **ባህላዊ ቅርሶች እንደ መዝናኛ ምንጭ ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ።**

3. ባህላዊ ቅርሶችን መጠበቅ የመንግስት እና የሁሉም ሰው ሃላፊነት ነው።
4. ባህላዊ ቅርሶች ሊበላሹ የሚችሉት በሰው ሰራሽ አደጋ ብቻ ነው።
5. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ስንደቅ አላማ የባህል ቅርሶቻችን አካል ነው።